ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ-ሙስና ቅፅ 1 ቁጥር 18 ታህሳስ 30/2016 ዓ.ም

# በኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ(ዶ/ር) የተመራ የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን በተመድ የፀረ-ሙስና ስምምነት የአባል አገራት ጉባዔ ላይ ተሳተፈ







በፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ(ዶ/ር) የተመራ የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን በአሜሪካ አትላንታ ከተማ በተካሄደው የተመድ የፀረ-ሙስና ስምምነት የአባል አገራት ጉባዔ ላይ ተሳትፎ አድርገዋል፡፡ ጉባኤው የአባል አገራት የፀረ-ሙስና ስምምነት አፈጻጸም ላይ ውይይት ያደረገ ሲሆን አባል አገራት በፀረ-ሙስና ትግል ትብብር ለማጠናከር የሚያግዙ ምክክሮችን አድርገዋል። በጉባኤው ኢትዮጵያም አገራዊ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ሪፖርት በኮሚሽኑ በኩል አቅርባለች።

በየሁለት ዓመት የሚካሄደውን ዓለምአቀፍ የፀረ-ሙስና ጉባኤ ኢትዮጵያ የምታዘጋጅበት ዕድል እንዲሰጥ ኮሚሽነሩ ጥያቄ ያቀረቡት ሲሆን፣ በኮንፈረንሱ ሥራ አስፈጻሚ ለማየት አወንታዊ ምላሽ ተገኝቷል። በሌላ በኩል ከአገር የሚሸሽ ሀብት ለማስመለስ የአገራትን ትብብር የሚያጠናክሩ የጎንዮሽ ምክክሮች በጉባኤው ሀገራት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን በመከላከል፣ ተጠያቂነትን እና ግልፅነትን በመፍጠር እንዲሁም በተቋማት ላይ ያለውን ሙስናን የመዋጋት ቁርጠኝነት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የጋራ ግንዛቤ በማስያዝ ንቅናቄ መፍጠር እንደሚገባ አቅጣጫ መቀመጡ ተመላክቷል። በጉባኤው ሙሰኞችን በድርጊታቸው ተጠያቂ በማድረግ፣ መንግስታት ለዜጎቻቸው ምላሽ ሰጪ እና የተጠያቂነት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን፥ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ወጣቶችን ያሳተፈ መሆን እንዳለበት ተጠቁሟል። በጉባኤው የተሳተፉ ወጣቶች ሙስና እና ብልሹ አሰራር እየተበራከተ በመምጣቱ የችግሩ ተጠቂዎች መሆናቸውን ገልፀው፥ የሙስና ሰለባ እንደመሆናችን መጠን ችግሩን ለመፍታት የበኩላችንን ድርሻ መወጣት አለብን ማለታቸው ተገልጿል።

በጉባኤው የፀረ-ሙስና ማዕቀፎችን ውጤታማነት፣ ዓለምአቀፍ ትብብርን መፍጠር እና የስምምነት አፈፃፀምን እንዲሁም የተደራጁ የሙስና ወንጀሎችን በጋራ መከላከል እና የጠቋሚዎችን ከለላ ማስጠበቅ የሚሉ ጉዳዮች ተነስተው የጋራ አቋም ተይዞባቸዋል።

ሙስና በአየር ንብረት ለውጥ ቅነሳ፣ በአለማችን የበለፀገ ብዝሃ ህይወት ጥበቃ ላይ ያለው ተጽእኖ፣ ከህገ ወጥ ማዕድን ማውጣት፣ የደን መጨፍጨፍ እና አረንጓዴ ሽግግር እና ሌሎችም ጉዳዮች ላይም ተፅዕኖው የጎላ በመሆኑ በጋራ መከላከል እንደሚገባ ውይይት እንደተደረገባቸው ተመላክቷል።

በአሜሪካ አትላንታ ከተማ ከታህሳስ 1-5/2016 ዓ.ም የተካሄደው አስረኛው የተመድ የፀረ-ሙስና ስምምነት የአባል አገራት ጉባዔ ሁለተኛውን የአተገባበር ግምገማ ወደ ሰኔ 2026 በማራዘም እና በ2025 የሚካሄደውን አስራ አንደኛውን ጉባኤ ኳታር እንድታስተናግድ ውሳኔ በማሳለፍ ጉባኤው ተጠናቋል። በጉባኤው ከ160 ሀገራት የተውጣጡ ከ2,000 በላይ የመንግስት ተወካዮች እና ከ900 በላይ የሲቪል ማህበራት እንዲሁም የግሉ ሴክተር እና ወጣቶች የተሳተፉ ሲሆን፥ በመድረኩ ከፍተኛ ተሳትፎ መታየቱን ተገልጿል።



## ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት መፍጠር የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከር የጎላ ሚና አለው

ክቡር ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር)

ገፅ - 2

## በክልሉ የተጀመረው የሀሰተኛ ትምህርት መረጃ ማጥራት ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል

አቶ አስራት አዳሮ

ገፅ - 10

## ብልሹ አሰራርን በመከላከል የፀረ-ሙስና ትግሉን ማስቀጠል እና ህገወጥ የመሬት ወረራን መከላከል ላይ አመራሩ ትኩረት አድርጎ መስራት አለበት

አቶ እንዳሻው ጣሰው





በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ብልሹ አሰራርን በመከላከል የፀረ-ሙስና ትግሉን ማስቀጠል እና ህገ-ወጥ የመሬት ወረራን መከላከል ላይ አመራሩ ትኩረት አድርጎ መስራት እንዳለበት የክልሉ ርዕሰ-መስተዳድር አቶ እንዳሻው ጣሰው ገለጹ። በክልሉ በመቶ ቀናት እቅድ አፈጻጸም እና በቀጣይ መቶ ቀናት እቅድ ላይ ትኩረት ያደረገ የውይይት መድረክ በሆሳዕና ከተማ ተካሂዷል።

አቶ እንዳሻው ጣሰው በውይይት መድረኩ ላይ እንደገለጹት በክልሉ ከዚህ ቀደም በተካሔዱ የህዝብ መድረኮች በቂ ግብዓት ማሰባሰብ እንደተቻለ ገልፀው፥ ይህም የሚነሱ የልማት እና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መለየት ያስቻለ ስለመሆኑም አብራርተዋል። ከአፈር ማዳበሪያ ስርጭት ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ችግሮችን ማረም ይገባል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፥ በዘርፉ የሚስተዋለውን ብልሹ አሰራር የማረም ስራ እንደሚከናወንም ጠቁመዋል። በክልሉ የገቢ አሰባሰብ ስርዓትን ማዘመን፣ ብልሹ አሰራርን መከላከል፣ የፀረ-ሙስና ትግሉን ማስቀጠል እና ህገወጥ የመሬት ወረራን መከላከል ላይ አመራሩ በትኩረት እንዲሰራም አሳስበዋል።

## ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት መፍጠር የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከር የጎላ ሚና አለው

ክቡር ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር)





የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ከኮሚሽኑ የሥራ ክፍል መሪ ስራ አስፈፃሚዎች እና ዴስክ ኃላፊዎች እንዲሁም ከ25 የዘርፍ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አስፈፃሚዎች ጋር በአዳማ ከተማ ውይይት አካሂዷል። በመድረኩ የዘርፎች የ20ኛ የዓለምአቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን አከባበር አፈፃፀም እና የዘርፎች የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ሥራ እንቅስቃሴ ላይ የሱፐርቪዥን ሪፖርት ግምገማ ተካሂዷል።

በመድረኩ የተገኙት የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ እንደገለፁት ሙስና ለሀገር መሠረታዊ ችግር በመሆኑ መከላከል ላይ ትኩረት ተደርጎ መሰራት እንዳለበት ያሳሰቡ ሲሆን፥ እያንዳንዱ ዘርፍ በራሱ አቅም ሙስናን አስቀድሞ በመከላከል አስተዳደራዊ ተልዕኮውንም መወጣት አለበት ብለዋል። ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት መፍጠር የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከር የጎላ ሚና ያለው መሆኑንም ገልፀዋል።

በውይይቱ ተገኝተው ከመድረኩ ለተነሱት ጥያቄዎች ምላሽ የሰጡት የኮሚሽኑ ም/ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ በበኩላቸው ሙስና ውስብስብ ወንጀል በመሆኑ ሥራዎችን በተቀናጀ መልኩ የአቅም ግንባታ ክፍተቶችን በመሙላት ልንሰራ ይገባል ብለዋል። በተመሳሳይ እቅዶቻችን በመናበብ መስራት አላማን ከግብ ለማድረስ እንደሚረዳ የገለፁት ም/ኮሚሽነር አቶ እሸቴ አስፋው፥ ሁሉም ዘርፎች ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ኃላፊነት እና ግዴታ እንዳለባቸው አስገንዝበዋል። የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ እስታንዳርድ እየወጣ መሠራት አለበትም ብለዋል።

በመድረኩ ኮሚሽኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት እንዳለበት ትኩረት ከተሰጡት ጉዳዮች መካከል አንዱ ሲሆን፥ የትውልድ ሥነምግባር ግንባታ፣ የሙስና ጥናት ግኝቶች እና የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስልጠናዎች በትኩረት ተዳሰዋል።

በተመሳሳይ ኮሚሽኑ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ በሆኑ አምስት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሙስና መከላከል ጥናት ፕሮፖዛል ቀርቦ ውይይት ተደርጎባቸዋል። ጥናት ሊካሄድባቸው የተመረጡ እና ፕሮፖዛል የተዘጋጀላቸው አምስቱ ርዕሰ ጉዳዮች በአገራችን የገቢ ግብር እና ታክስ አሰባሰብ የሙስና እና ብልሹ አሠራር ወንጀል ድርጊቶች መንስኤዎችና መፍትሔዎች፣ በአገራችን የጉምሩክ አሠራር ሥርዓት እና የኮንትሮባንድ እርምጃዎች ውጤታማነት፣ በአገራችን የወጪ እና ገቢ ንግድ የዉጭ ምንዛሪ አስተዳደር የአሠራር ሥርዓት ግልጽነት እና ተጠያቂነት፣ የመንግሥት ግዥ አገልግሎት አሠራር ሥርዓት ግልጽነት እንዲሁም በአገራችን የዉጭ አገር የሰራተኞች ስምሪት አሠራር ሥርዓት ግልጽነት እና የሰራተኞች ተጠቃሚነት የሚሉ ናቸው። ከመድረኩ በቀረበው ጥያቄ እና አስተያየት ላይ በኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች ማብራሪያ የተሰጠ ሲሆን፣ በፕሮፖዛሎች ላይ የተሰጡት አስተያየቶችን በማካተትና በማሻሻል የሙስና መከላከል ጥናት እንደሚካሄድ አቅጣጫ ተሰጥቷል።

## ሀሰተኛ የማንነት ሰነድ በመጠቀም በህገወጥ መልኩ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ዜጎች ከጥር አንድ ጀምሮ ወደህጋዊ መስመር እንዲገቡ የጊዜ ገደብ ተሰጠ

ሀሰተኛ የማንነት ሰነድ በመጠቀም በህገወጥ መልኩ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ዜጎች ከጥር አንድ እስከ ጥር 30 2016 ዓ.ም ድረስ ወደህጋዊ መስመር እንዲገቡ የጊዜ ገደብ መሠጠቱን የኢሚግሬሽንና የዜግነት አገልግሎት አስታወቀ። ከተፈቀደላቸው የጊዜ ገደብ በላይ የሚኖሩና በህጋዊ መስመር ያልገቡ የተለያዩ ሀገራት ዜጎች መኖራቸውንም ገልጿል። ሀሰተኛ የማንነት ሰነድ በመጠቀም በሕገወጥ መልኩ በኢትዮጵያ የሚኖሩና የሌላ ሀገር ዜግነት ያላቸው አካላት ወደህጋዊ መስመር የማስገባት ስራን አስመልክቶ ለመገናኛ ብዙኃን መግለጫ ተሰጥቷል።




የኢሚግሬሽንና የዜግነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ሰላማዊት ዳዊት በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በርካታ የውጭ ሀገር ዜጎች ሀሰተኛ ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ፣ ሀሰተኛ ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ፣ ሀሰተኛ ፓስፖርት፣ ሀሰተኛ ቪዛ እና ሀሰተኛ ሰነድ አዘጋጅተው በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች እየኖሩ ይገኛሉ።

በተደረገው የማጣራት ስራ ከ18 ሺህ በላይ ሀሰተኛ ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ፣ ከ1ሺህ 500 በላይ ሀሰተኛ ቪዛ እና ከአንድ ሺህ 800 በላይ የትውልደ ኢትዮጵያዊ መታወቂያን ያሰሩ ዜጎች በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች መገኘታቸውን አስታውቀዋል። እነዚህንና ሌሎች ህገወጥ ሰነድ ያለቸው ዜጎች ከጥር አንድ ቀን 2016 ዓ.ም እስከ ጥር 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ወደ ተቋሙ በመምጣት ህጋዊ ሰነድ እንዲዘጋጅላቸው የማያደርጉ ከሆነ እርምጃ ይወሳዳል ብለዋል። በሕገወጥ መልኩ በኢትዮጵያ የሚኖሩ እና የሌላ ሀገር ዜግነት ባላቸው አካላት ላይ በተጠቀሰው ጊዜ ህጋዊ ሰነድ እንዲዘጋጅላቸው ካለደረጉ መንግስት እርምጃ እንደሚወሰድ ገልጸዋል።

## በወላይታ ሶዶ ከተማ በሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ ሁለት ግለሰቦች በቁጥጥር ስር ዋሉ



በህግ ቁጥጥር የዋሉት ሁለት ግለሰቦች በወላይታ ሶዶ ከተማ የንግድና ገበያ ልማት ጽ/ቤት ባለሙያዎች ናቸው። ግለሰቦቹ በአገልግሎት መሥሪያ ቤቱ የተሰጣቸውን የመንግስትና የህዝብን አደራ ወደ ጎን በመተው ከተገልጋይ ገንዘብ ሲቀበሉ እጅ ከፈንጅ ተይዘው በቁጥጥር ስር ነው የዋሉት። ተጠርጣሪዎቹ ከፍተኛ ገንዘብ በመጠየቅ በሙስና ተግባር መሰማራታቸውንና የግል ጥቅማቸውን ሲያሳድዱ ነበር።

በከተማው መሃል ቀበሌ የአንዲት ነጋዴ የንግድ ቦታ በማሸግ ገንዘብ ካልሰጠሽ አይከፈትም በማለት ተደራድረው ገንዘብ ሲቀበሉ ከተበዳይ በደረሰው ጥቆማ የመሃል ቀበሌ ፖሊስ እጅ ከፍንጅ በመያዝ በቁጥጥር ስር ውለዋል። ስለሆነም ህበረተሰቡ እንዲህ አይነት ጥቆማ ለህግ አካላት በመሰጠት ብልሹ አሰራሮችንና ሌብነት ማጋለጥ እንደሚገባ ጥሪ ቀርቧል።

## ከፓስፖርት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የሚታዩ ብልሹ አሰራሮች እንዲታረሙ አመራሩ እና ሰራተኛው በየጊዜው የሚፈጠሩ ችግሮችን በመፍታት ቅንጅታዊ አሰራራቸውን ሊያጠናክሩ እንደሚገባ ተጠቆመ





ከፓስፖርት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የሚታዩ ብልሹ አሰራሮች እንዲታረሙ አመራሩ እና ሰራተኛው በየጊዜው የሚፈጠሩ ችግሮችን በመፍታት ቅንጅታዊ አሰራራቸውን ሊያጠናክሩ እንደሚገባ ተጠቆመ

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የህግና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከፓስፖርት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የሚታዩ ብልሹ አሰራሮች እንዲታረሙ አመራሩ እና ሰራተኛው በየጊዜው የሚፈጠሩ ችግሮችን በመፍታት ቅንጅታዊ አሰራራቸውን ሊያጠናክሩ እንደሚገባ አሳስቧል። ቋሚ ኮሚቴው በሶማሌ ክልላዊ መንግሥት የሚገኘውን የኢምግሬሽን ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት ተመልክቷል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ እፀገነት መንግስቱ ተቋሙ የመረጃ ልውውጥ ስርዓቱ ተስማሚ በሆነ ቴክኖሎጂ እንዲታገዝ በማድረግ በሀሰተኛ ሰነድ ወደ ሀገር የሚገቡትንም ሆነ የሚወጡ ዜጎችን ለመቆጣጠር ድንበር አካባቢ ጥንቃቄ በማድረግ ህግና ስርዓት እንዲከበር በትኩረት መስራት ይገባል ብለዋል።

ከፓስፖርት አሰጣጥ ጋር በተያያዘም የሚታዩ ብልሹ አሰራሮች እንዲታረሙ አመራሩ እና ሰራተኛው በየጊዜው የሚፈጠሩ ችግሮችን በመፍታት ቅንጅታዊ አሰራራቸውን ሊያጠናክሩ እንደሚገባም ሰብሳቢዋ አስገንዝበዋል። በተቋሙ የቅሬታ እና የብልሹ አሰራር ምንጮችን ለይቶ ለማድረቅ ከፌደራል እና ከክልል ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ መስራት እንደሚያስፈልግም አመላክተዋል።

የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ተጠባባቂ አስተባባሪ ሳራ ጃማ በበኩላቸው ተቋሙ በጀመራቸው የሪፎርም ስራዎች ተደራሽነታቸው ላይ የታዩ መልካም ለውጦች መኖራቸውን ገልጸው፥ ተጠያቂነትን ከማምጣትና ብልሹ አሰራርን በመታገል መንግስት የጀመራቸውን ስራዎች ሊያጠናክር ይገባል ብለዋል። መታወቂያን ዲጂታላይዝ በማድረግ ሀሰተኛ ማስረጃን እና ብልሹ አሰራርን የምንከላከልበት ስርዓት በመዘርጋት እንዲሁም በድንበር አካባቢ የመለያ መታወቂያ በማዘጋጀት ተቋሙ የተሻለ ለውጥ እንዲያመጣ ቋሚ ኮሚቴው ሊደግፈን ይገባል ነው ያሉት። ቋሚ ኮሚቴው በበኩሉ ተገልጋዩ የሚፈልገውን አገልግሎት ሳይጉላላ እንዲያገኝ ከማድረግም ባሻገር ደህንነቱ የተረጋገጠ አገልግሎት እንዲያገኝ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት እንዲኖር በትኩረት ሊሰራ እንደሚገባ አሳስበዋል።

## የኮሚሽኑ አመራርና ሠራተኞች የ2016 በጀት አመት የ6 ወር የስራ አፈፃፀም ግምገማ አካሄዱ







የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮች እና ሰራተኞች የ2016 በጀት ዓመት የ6 ወር የስራ አፈፃፀም ግምገማ አካሄደዋል። የኮሚሽኑ የግማሽ ዓመቱ እቅድ ክንውን የቀረበ ሲሆን፥ በሁሉም ዘርፎች መልካም የሚባል ውጤት የተገኘበት መሆኑ ተመላክቷል።

በተቋማዊ አቅም ግንባታ እና አስተዳደር ድጋፍ ዘርፍ፣ በአሰቸኳይ ሙስና መከላከል፣ በሥነምግባር ግንባታ፣ በጥቅም ግጭት መለየትና ማጣራት፣ በሙስና መረጃ አያያዝ እና የሙስና መከላከል ሥራን ውጤታማ የማድረግና በዘርፍ ተቋማት ላይ የሚገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን የመደገፍና አቅም ግንባታ የመስጠት እንዲሁም የፀረ-ሙስና ትግሉን የተሳለጠ በማድረግ በርካታ ስራዎች መሰራታቸው ከቀረበው ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል። እንዲሁም አቅምን ከመገንባት አኳያ የተለያዩ ስልጠናዎች እና ግንዛቤ የመፍጠር ስራ የተሰራ ሲሆን፣ በመልካም አስተዳደር ጉዳዮች የታዩ ክፍተቶችን እስከ ተቋማት ድረስ በመሄድ ለመፍታት መሞከሩ ተገልጿል።

በቀረበው የ6 ወር አፈፃፀም በርካታ ተግባራት መሰራታቸውን እና ለቀጣይ እቅድ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት መሰራት እንዳለበት የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ አሳስበዋል። በተመሣይ ምክትል ኮሚሽነር አቶ እሸቴ አስፋው ከተሳታፊዎች ለተነሡ አስተያየቶች እና ጥያቄዎች ምላሽ የሰጡ ሲሆን እስካሁን የተሰሩት ተግባራት እንደ እቅድ ጥሩ አፈፃፀም የታየበት መሆኑን ጠቁመው፥ ለቀጣይ ስራ በቁርጠኝነት እና በተነሳሽነት መንፈስ በጋራ መስራት እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

## በሙስና ለመዘበር የነበረን መሬት እና ገንዘብ ማስቀረቱን የአማራ ክልል ፍትሕ ቢሮ አስታወቀ



በአማራ ክልል የተለያዩ ከተሞች በሙስና ሊመዘበር የነበረን መሬት እና ጥሬ ገንዘብ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ማስመለስ መቻሉን የክልሉ ፍትሕ ቢሮ አስታውቋል። የአማራ ክልል ፍትሕ ቢሮ ምክትል ኃላፊ አያሌው አባተ(ዶ.ር) ለቢሮው ሠራተኞች ከአጋር አካላት ጋር በነበረው መድረክ ለውይይት መነሻነት ባቀረቡት ጽሑፍ እንደገለፁት በባሕር ዳር ከተማ ከመሬት የሊዝ የውል ስምምነት ጋር ተያይዞ ለመንግሥት መግባት የነበረበት፣ ነገር ግን ግለሰቦች ሊበለጽጉበት የነበረን 273 ሚሊዮን 744 ሺህ 101 ብር በጥብቅ ክትትል እና በቅንጅታዊ አሠራር ማስመለስ መቻሉን አብራርተዋል።

የጨረታ አሸናፊ ላልኾኑ ግለሰቦች በረቀቀ የሙስና ዘዴ ሊተላለፍ የነበረን 50 ሚሊዮን ብር ማስመለስ ተችሏል ያሉት ዶክተር አያሌው፥ 952 ሺህ 666 ካሬ ሜትር ቦታም ከሙስና በመታደግ ለመንግሥት ገቢ ተደርጓል ብለዋል። ምክትል ኃላፊው እንዳሉት በሰሜን ሸዋ ዞን የደብረ ብርሃን ከተማ ፍትሕ ቢሮ ከአጋር አካላት ጋር በመቀናጀት በሰራው ሥራ 193 ሰዎች በህሰት "በማህበር ተደራጅተናል" በማለት በተወሳሰበ መንገድ ሊዘርፉት የነበረን 926 ሺህ 400 ካሬ ሜትር መሬት ወደ መሬት ባንክ ገቢ እንዲኾን ተደርጓል።

በይልማና ዴንሳ ወረዳም "እጃቸውን እግር አድርገው" የሚታተሩ አርሶ አደሮች ያቋቋሙትን "አበሽ ግላ" የተባለ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማኅበርን ሙሰኞች በረጅም እጃቸው ለዘረፋ መንገዱን እያመቻቹ መኾናቸውን ከኅብረተሰቡ ለፖሊስ እና ዐቃቢያን ሕግ ጥቆማ ደርሷቸው የፍትሕ አካሉም ጥቆማውን መሠረት አድርጎ ጉዳዩን በጥንቃቄ ተከታትሎ እንደደረሰበት ገልጸዋል። ከገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማኅበር 6 ሚሊዮን 350 ሺህ 91 ብር ሙሰኞች በየግል የባንክ የሒሳብ ደብተራቸው ላይ አስገብተው በአቋራጭ ለመበልጸግ ሲሯሯጡ መያዙንም ዶክተር አያሌው ተናግረዋል።

በአማራ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን የሙስና ወንጀሎች ምርመራ ምክትል ዘርፍ ኀላፊ ረዳት ኮሚሽነር መላኩ ሲሳይ እንዳሉት አሁን ላይ በአብዛኛው አካባቢ የጸጥታ ችግር ኑሮ እንኳ ጥቆማ የሚያቀርበው የኅብረተሰቡ ክፍል ቁጥሩ ከፍተኛ መኾኑ ሙስናን በጋራ ከሰራን መከላከል እንደሚቻል የሚያሳይ ነው ብለዋል። የሙስና ወንጀል እንደሌሎቹ መደበኛ ወንጀሎች በሰው ምስክር የሚያልቅ አይደለም፥ በዋነኛነት የሠነድ ማስረጃን ይፈልጋልና ጠቋሚዎች የሚያገኟቸውን ሠነዶች በጥንቃቄ መያዝ እንዳለባቸውም ተናግረዋል።

የምክክር መድረኩ ተሳታፊዎች እንዳሉት ሙስናን "ሁሉም ሠው በያገባኛል ስሜት ከሠራ" ሙሉ በሙሉ ማጥፋት ባይቻልም መቀነስ ይቻላል። ለዚህ ደግሞ ከፍትሕ አካል ጋር ለመሥራት መዘጋጀታቸውን ተናግረዋል። ሙስናን መከላከል የሚቻለው በቁርጠኝነት በመሥራት ብቻ ነው፤ ስለዚህ ሁሉም ከቤቱ ጀምሮ ሙስናን የሚጸየፍ ትውልድ ለማነጽ ቁርጠኛ ኾኖ መሥራት ይገባዋል ብለዋል።

## የክልሉን ሁለንተናዊ ዕድገት ሊያደናቅፋ የሚችሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን በንቃት መከላከል ጊዜው የሚጠይቀው ተግባር ነው - ኮሚሽኑ





የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በክልሉ ለሚገኙ የዞን፣ የከተማና የወረዳ የሥነ-ምግባር መከታተያ ባለሙያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በወላይታ ሶዶ ከተማ ሰጥቷል። የፀረ-ሙስና ትግሉ ከተጀመረ ዘመናትን ያስቆጠረ ቢሆንም በሀገሪቱ ዕድገትና ብልፅግና ላይ እስከአሁን እያሳደረ ያለው ተፅእኖ ከፍተኛ መሆኑ ይነገራል። ይህን ተከትሎ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራውን ጨምሮ በሙሰኞች ላይ እየተወሰደ ያለው እርምጃ ጠንካራ ሊሆን ይገባል።

በክልሉ ሁለንተናዊ ዕድገትና ብልፅግና ላይ እንቅፋት ሊፈጥር የሚችለውን የሙስና እና ብልሹ አሰራርን ፈር ለማሲያዝ የታሰበለት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በሚጀመርበት ወቅት የክልሉ የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ሶፊኒያስ ደስታ ኮሚሽኑ በክልሉ በሁሉም ዘርፎች የሚስተዋሉ የሥነ-ምግባር እና ብልሹ አሰራሮችን ለመጋፈጥ በሚያስችል ቁመና ላይ እንዳለም አስታውቀዋል። በይበልጥ ከመሬት ወረራና ተያያዥ ጉዳዮች ጋር ከዚህ ቀደም የነበረው ብልሹ አሰራር ክልሉን እየተፈታተነው ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፥ ይህንን ተከትሎ ቀድሞ የመከላከልና ብልሹ አሰራሩ ተፈጥሮ ሲገኝ የማጣራትና የህግ እርምጃ የሚወሰድበትን ሂደት መጀመሩንም አስታውቀዋል።

ኮሚሽኑ በአዲስ መልክ ከተዋቀረ በኋላ አስር የተለያዩ ጥቆማዎች የደረሱት ሲሆን፣ በእነዚህም ላይ የማጣራት ሥራ እየተሰራባቸው ስለመሆኑ የጠቆሙት ኮሚሽነር ሶፍኒያስ፣ የማጣራት ሥራው ሲጠናቀቅም ጥፋተኞች ላይ የማያዳግም እርምጃም እንደሚወሰድባቸውም ተናግረዋል። የክልሉን ሁለንተናዊ ዕድገትና ብልፅግና ሊያደናቅፉ የሚችሉ ብልሹ አሰራሮችን በንቃት መከላከል ጊዜው የሚጠይቀው ተግባር ነውም ብለዋል።

በስልጠናው ላይ ተሳታፊዎች በበኩላቸው አዲስ የተሻሻለው የኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ከዚህ ቀደም የነበረውን የሙስና እና ብልሹ አሰራር ትግልን የበለጠ የሚያጠናክርና ለዘርፉ ባለሙያዎች አቅም እንደሚሆናቸውም ተናግረዋል። በወላይታ ሶዶ ከተማ የተሰጠ ሥልጠና ብልሹ አሰራሮችንና በይበልጥ ከግዥ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሴብነቶች ከመከሰታቸው በፊት አስቀድሞ ለማክሰም የሚረዳ አቅም እንደሚፈጥርላቸው ተናግረዋል።

## ኮሚሽኑ ለመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመራሮች በሥነምግባራዊ አመራር እና በግዥ ላይ የሚፈፀም ሙስና መከላከል ላይ ያተኮረ የአቅም ግንባታ ስልጠና ሰጠ



የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በአራት የሥልጠና መዓከላት ከተለያዩ አጎራባች ዩኒቨርስቲዎች ለተውጣጡ አመራሮች በሥነምግባራዊ አመራር እና በግዥ ላይ የሚፈፀም ሙስናን መከላከል ላይ ያተኮረ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል።

ከስድስት አጎራባች ዩኒቨርስቲዎች ለተወጣጡ ሰልጣኞች በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ዋናው ግቢ በተሰጠው ስልጠና የተገኙት የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ አስተዳደርና ልማት ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ሳሙኤል ጂሎ እንደተናገሩት ስልጠናው በሀገር ደረጃ በአራት ክላስተሮች ተከፋፍሎ በሀዋሳ፣ በድሬዳዋ፣ በአርባምንጭ እና በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲዎች እየተሰጠ መሆኑን ገልፀው፥ ዓላማዉም በመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በግዢ ላይ የሚፈፀም ሙስናን ለማስቀረት እንዲሁም ሙስናን መከላከል ላይ ትኩረት ያደረገ የግንዛቤ ማስጨበጫ መሆኑን አመላክተዋል።





ዶ/ር ሳሙኤል ጂሎ አክለውም ስልጠናው አስቸኳይ የሙስና መከላከል ስርዓትን፣ በግዢ ሂደት ላይ የሚፈፀም ሙስና እና የሙስና አጠራጣሪ ምልክቶችን እንዲሁም የመከላከያ ስልቶችን ያከተተ መሆኑን ጠቅሰው፥ በግዢ ስርዓቱ የሚፈፀም ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከልና ክፍተቶችንም ለመድፈን ይህን መሰል ስልጠና በመስጠት አቅምን ማጎልበት አስፈላጊ መሆኑን አሳስበዋል።

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የስልጠና ባለሙያ ወ/ሮ ኃይማኖት ገ/እግዚሔብር ስልጠናውን በሚሰጡበት ወቅት እንደተናገሩት የስልጠናው ዓላማ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አርዓያነት ያላቸውን የአመራር ክህሎት በማጎልበት ሙስና እና ብልሹ አሠራሮችን የሚጠየፍ ዜጋን በማፍራት ረገድ የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ ለማጎልበት መሆኑን ገልፀው፥ ኮሚሽኑ በ25 የመንግስት ሴክተር መስሪያ ቤቶች ላይ ባደረገው ጥናት በግዥ ስርዓት አፈጻጸም ላይ ክፍተቶች መኖራቸው ተናግረዋል። ከነዚህም መካከል የትምህርት ሴክተር አንዱ መሆኑንና ድርጊቱን ለመከላከል ስልጠናው ማስፈለጉን አስረድተዋል።

ለሁለት ቀናት በተሰጠው ስልጠና በማዕከልነት የተመረጠውን ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ ከዲላ፣ ከአርሲ፣ ከቡሌ ሆራ እና ከመደወላቡ እንዲሁም ከቦረና ዩኒቨርስቲ የተወጣጡ 78 የአስተዳደርና ልማት ም/ፕሬዝዳንቶች፣ የፋይናንስ፣ የግዢና ንብረት አስተዳደር፣ የዉስጥ ኦዲት፣ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ዳይሬክተሮች፣ የተማሪዎች አገልግሎት ዲኖች፣ የግንባታ ፕሮጀክት ስራ አስኪያጆችና ከፋይናንስ፣ ግዢና ንብረት ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ስራ አስፈፃሚዎች መሳተፋቸዉ ተገልጿል።

በተመሳሳይ ከወልቂጤ፣ ከወራቤ፣ ከዋቸሞ፣ ከወላይታ ሶዶ፣ ከጂንካ እና ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲዎች ለተወጣጡ የሥራ ኃላፊዎች በአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ ለሁለት ቀናት በክላስተር መሰጠቱ ተገለጿል። የሥልጠናው ዓላማ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በግዥ ላይ የሚፈጸመውን ሙስና የመከላከል አቅምን በማሳደግ ከሙስና እና ብልሹ አሠራር የጸዳ የግዥ ሥርዓት እንዲከተሉ ማስቻል ነው ተብሏል።

በመንግስት ግዥ ላይ የሚፈጸም ሙስናን መከላከል እና በሥነምግባራዊ አመራር ላይ ትኩረት ያደረገውን የአቅም ግንባታ ስልጠና በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የስልጠና ዴስክ ኃላፊና ባለሙያዎች መሰጠቱ ተገልጿል። በስልጠናው ከስድስቱ ዩኒቨርስቲ የተውጣጡ የግዥና ንብረት እንዲሁም የፋይናንስና በጀት አስተዳደር ኃላፊዎች፣ ቡድን መሪዎችና ባለሙያዎች፣ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና መከታተያ ክፍል ሥራ አስፈጻሚዎች፣ የተማሪዎች አገልግሎት ኃላፊዎች፣ የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ሌሎች የሚመለከተቸው አካላት ተሳታፊ መሆናቸውን ተገልጿል።

በተመሳሳይ በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ማዕከልነት በምስራቁ የአገራችን ክፍል ከሚገኙ የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ለተውጣጡ የተለያዩ አመራሮች በመንግስት ግዥ ላይ የሚፈጸም ሙስናን መከላከል እና በሥነምግባራዊ አመራር ላይ ያተኮረ ስልጠና በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የስልጠና ዴስክ ኃላፊና ባለሙያዎች ለሁለት ቀናት ተሰጥቷል። ከአምስት ዩኒቨርሲቲ ለተወጣጡ አመራሮች በተሰጠው ስልጠና የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ የቀብሪዳህር፣ የጅግጅጋ እና የሀረማያ እንዲሁም የኦዳቡልቱም ዩኒቨርሲቲ የሥራ ኃላፊዎች ተሳትፈውበታል።

በተመሳሳይ ዜና በሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ለስድስት የመንግስት የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አመራሮች የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል። በስልጠናው የተገኙት የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር አህመድ ሙስጠፋ በመክፈቻ ንግግራቸው እንደገለፁት አመራሩ በሥነምግባር በመታነጽ በዩኒቨርስቲያቸው ውስጥ በግዥ ላይ የሚፈጸምን ሙስና የመከላከል አቅምን በማሳደግ ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የጸዳ የግዥ ስርዓት እንዲከተሉ ለማስቻል የተዘጋጀ ስልጠና በመሆኑ ሰልጣኞች ትኩረት አድርገው እንዲከታተሉ አሳስበዋል። ስልጠናው በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የስልጠና ዴስክ ኃላፊና ባለሙያዎች የተሰጠ ሲሆን፤ በመንግስት ግዥ ላይ የሚፈጸም ሙስናን መከላከል እና በሥነምግባራዊ አመራር ላይ ያተኮረ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል።

ስልጠናው በሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ ለሁለት ቀናት የተሰጠው ሲሆን፤ ከጅማ፣ ጋምቤላ፣ ቦንጋ፣ መቱ እና ወለጋ ዩኒቨርሲቲዎች የተውጣጡ የአስተዳደርና ልማት ም/ፕሬዝዳንቶች፣ የፕሬዝዳንት ጽ/ቤት፣ የፋይናንስ፣ የግዥ፣ የንብረት እና የቢዝነስና ገቢ ማመንጫ ስራ አስፈጻሚዎች፤ የውስጥ ኦዲት እና የተማሪዎች መሠረታዊ አገልግሎት እንዲሁም የግንባታ መሠረተ-ልማት ኃላፊዎች ተሳታፊ መሆናቸውን ተመላክቷል። በአራቱም የሥልጠና ማዕከላት ከ23 ዩኒቨርስቲዎች የተወጣጡ 276 የሥራ ኃላፊና ሰራተኞች ተሳታፊ መሆናቸው ተገልጿል።

## የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በማሕበር ለተደራጁ አካላት የሚደረገው የመሬት አሰጣጥ ግልፅና ተጠያቂነት ባለው አኳኋን መፈፀም እንዳለበት አስታወቀ




የክልሉ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽር አቶ መንግስቱ ላሎ በዘርፉ የሚስተዋሉ የአሰራር ክፍተቶችን ለመዝጋትም ግልፅና ተጠያቂነት ያለው አሰራር መዘርጋት፣ ደንብና መመሪያዎችን አክብሮና ጠብቆ መስራት ሁነኛ መፍትሄ መሆኑን ገልፀዋል። በዘርፉ የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮችን ለመዝጋትም ኮሚሽኑ ረዘም ያለ ጊዜ በመውሰድ በአሶሳ ከተማ አስተተዳር መሬት ልማት ማኔጅመንት የከተማ ቦታ አሰጣጥ ላይ ባደረገው የአሰራር ስርዓት ጥናት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር በር የሚከፍቱ 10 ግኝቶችን የጠቆመ ሲሆን፣ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ ምክረ ሐሳቦችንም አመላክቷል።

ጥናቱን ያቀረቡት በኮሚሽኑ የአሰራር ጥናት ኬዝ ቲም አስተባባሪ አቶ ፍቃዱ ሰብስቤ በዋናነት የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ክፍተቶች አገልግሎቶች እንዲጓተቱና ዘርፉ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ እንዲሆን መደረጉን አስረድተዋል። ችግሮችን ለመፍታትም አሰራሮችን በማዘመንና ከሰው ንክኪ በጸዳ መልኩ በቴክኖሎጅ መፈፀም፣ ስራውን በባለቤትነትና በተጠያቂነት መስራት የሚያስችሉ እንደ መሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ አሰራሮችን መዘርጋትና ለውጤታማነት መጠቀም እንደሚገባ ተጠቁሟል። በጥናቱ የተለዩ ምክረ ሃሳቦችንም መተግበር የሚያስችል የጋራ መግባባት ላይ መደረሱ ተገልጿል። በጥናት ግኝቱ ውይይት የአሶሳ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ አብዱልከሪም አብዱራሂም ጨምሮ የከተማ አስተዳድሩ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችና ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል።

## የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ መጽደቁ ተገለፀ






ለሁለት ቀናት በተካሄደው የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት 6ኛ ዙር 1ኛ አመት የስራ ዘመን 1ኛ መደበኛ ጉባኤ የተለያዩ ውሳኔዎችን በማሳለፍ ተጠናቋል። ጉባኤው የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅን ጨምሮ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት ተገምግመው ለህዝብ ምክር ቤት የተላለፉ የክልሉ መንግሥት የሚመራበት 27 አዋጆችን የክልሉ ህዝብ ምክር ቤት 6ኛ ዙር 1ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 1ኛ መደበኛ ጉባኤ አፅድቋል።

## ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ጉቦ የተቀበሉ የመሬት ሊዝ አስተዳደር ጽ/ቤት ሰራተኞች እጅ ከፍንጅ ተያዙ



በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ጉዳይ ለመፈፀም 1 ሚሊየን 4 መቶ ሺህ ብር ጉቦ የተቀበሉ ሁለት የመሬት ሊዝ አስተዳደር ፅ/ቤት ሰራተኞች እና ተባባሪያቸው በአዲስ አበባ ፖሊስ እና በብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት የቅንጅት ስራ እጅ ከፍንጅ ተይዘዋል። የክፍለ ከተማው ፖሊስ መምሪያ የወንጀልና ትራፊክ አደጋ ምርመራ ምክትል ዳይሬክተር ኮማንደር መስፍን በላቸው እንደገለፁት በቁጥጥር ስር የዋሉት ተጠርጣሪዎች የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ የመሬት አስተዳደር የቦታ ርክክብና ክትትል ቡድን መሪ እና የሊዝ ማስተላለፍ ባለሙያ ሲሆኑ፥ ሶስተኛዋ ተጠርጣሪ ደግሞ ለወንጀሉ ተባባሪ የሆነች የሊዝ ማስተላለፍ ባለሙያው እህት ነች።

የግል ተበዳይ ሐምሌ 3 ቀን 2015 ዓ.ም በሊዝ የገዙትን ቦታ ለመረከብ ሲመላለሱ ከቆዩ በኋላ የግንባታ ማስጀመሪያ ፈቃድ እንዲራዘምላቸው ለመጠየቅ አገልግሎት ፈልገው ነበር ወደ ክፍለ ከተማው አስተዳደር የሄዱት። ይሁን እንጂ ተጠርጣሪዎቹ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት ሲጠበቅባቸው ቀጠሮ በማብዛት ሲያመላልሷቸው እንደነበር እና ጉዳዩን ለመፈፀም ገንዘብ እንደተጠየቁ የግል ተበዳይ መግለጻቸውን ኮማንደር መስፍን አስረድተዋል። “በሊዝ የተገዛው ቦታ መንገድ ዳር በመሆኑ እኛ ለምንፈፅምልዎት ጉዳይ የሚከፍሉን ገንዘብ ይጨምራል” የሚል መደራደሪያ ሃሳብ በማቅረብ ተጠርጣሪዎቹ 3 ሚሊዮን ብር ጠይቀው እንደነበር እና በመጨረሻም ወደ 1 ሚሊዮን 5 መቶ ሺህ ብር ዝቅ እንደተደረገ ኮማንደር መስፍን አብራርተዋል።

ከተጠየቀው ገንዘብ ውስጥ 1 ሚሊዮን 2 መቶ ሺህ ብሩ የሊዝ ማስተላለፍ ባለሙያው በሆነው ተጠርጣሪ እህት የባንክ ሂሳብ ውስጥ እንዲገባ መደረጉን የጠቀሱት የምርመራ ሃላፊው፥ ከግል ተበዳይ በቀረበ አቤቱታ በአዲስ አበባ ፖሊስ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ ከብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ጋር በመቀናጀት ባደረጉት ክትትል 200 ሺህ ብር በጥሬ ገንዘብ ሲቀበሉ እጅ ከፍንጅ ተይዘው ምርመራ እየተጣራባቸው እንደሚገኝ ተገልጿል።





## ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰራተኞች የቴክኒክና የሥነ-ባህሪ ብቃት ፈተና መሰጠቱ ተገለፀ





በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርስቲ የተዘጋጀው እና ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰራተኞች በተሰጠው የቴክኒክና የሥነባህሪ ብቃት ፈተና 15 ሺሕ 592 ለሚሆኑ የከተማ አስተዳደሩ አመራሮች፣ ባለሙያዎች እና ሰራተኞች የተሰጠ መሆኑም ተጠቅሷል።

የሪፎርሙ ዋና ዓላማ በተቋማት የሚስተዋሉ የአሰራር ማነቆ፣ ሌብነት እና ብልሹ አሰራሮችን ለመዋጋት የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ለማስጠበቅ ፣ ተለማጭ የሆነ አደረጃጀት ለመፍጠር፣ አሰራሮችን ለማሻሻል፣ የስራ ተነሳሽነት እና ትጋት ያለው የሰው ኃይል ማፍራት ናቸው ተብሏል። ቴክኖሎጂ መር አገልግሎቶችን ከመስጠት ባሻገር አገልግሎቶቹን ለሶስተኛ ወገን በማስተላለፍ ቀልጣፋ እና ተደራሽ ግልጋሎትን በመስጠት ጊዜ፣ ገንዘብ፣ እንግልት እና የመልካም አስተዳደር ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ እየተሰራ ስለመሆኑም ተመላክቷል።



## በሐሰተኛ ሰነድ የይዞታ ካርታ አውጥቶ ሸጧል የተባለው ተከሳሽ በእስራትና በገንዘብ ተቀጣ



በሐሰተኛ ሰነድ 72 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ ካርታ አውጥቶ በ5 ሚሊየን ብር ሸጧል የተባለው ተከሳሽ ተፈራ አበራ ተከስተ በእስራትና በገንዘብ እንዲቀጣ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ የሙስና ወንጀል ችሎት ወሰነ። የፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ በተከሳሹ ላይ ተደራራቢ ክሶችን አቅርቦ ነበር።

በዚህም ባቀረበው 1ኛ ክስ ላይ ተከሳሹ የሙስና ወንጀልን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23 ንዑስ ቁጥር 1፣ ንዑስ ቁጥር 2/ሀ እና ንዑስ ቁጥር 3 ስር የተመላከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ስሙን ቀይሮ ሀሰተኛ የነዋሪነት መታወቂያ በመጠቀም በመስከረም 20 ቀን 2015 ዓ.ም በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 01 ስር የሚገኝ ጅምር ግንባታ ላይ የነበረ 72 ካሬ ሜትር የሆነ የሌላ ግለሰብን ይዞታ ሐሰተኛ ካርታ በማውጣት ሰናይት ሃይሌ ለተባለች ግለሰብ በ5 ሚሊየን ብር መሸጡን ጠቅሶ በክሱ ላይ አስፍሯል። በ2ኛ ክስ ላይ ዐቃቤ ሕግ በህገወጥ መንገድ የተገኘ ንብረትን ወይም ገንዘብን ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀል አዋጅ ቁጥር 780 አንቀጽ 29 ንዑስ ቁጥር 1 ሀ ስር የተመላከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ በህገወጥ መንገድ ያገኘውን ገንዘብ ምንጩን መደበቅ ወንጀል ፈጽሟል በማለትም ክስ አቅርቦበታል።

በሌላ በኩል ዐቃቤ ሕግ በዚሁ ተከሳሽ ላይ በ3ኛ ክስ የሙስና አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23 ንዑስ ቁጥር 1፣ ንዑስ ቁጥር 2/ሀ እና ንዑስ ቁጥር 3 ስር የተመላከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ በሐሰተኛ ሰነድ ካርታ የወጣለትን ይዞታ ለ3ኛ ሰው በተዘዋዋሪ ተሸጧል የሚል ክስ አቅርቦበት የነበረ ቢሆንም ይህ ክስ ከአንደኛ ክስ ጋር ተጠቃሎ እንዲቀርብ በፍርድ ቤቱ በመታዘዙ ተጠቃሎ እንዲታይ ተደርጓል። ተከሳሹ የክስ ዝርዝር ከደረሰው በኋላ ወንጀሉን አለመፈጸሙን ገልጾ የሰጠውን የዕምነት ክህደት ቃል ተከትሎ ዐቃቤ ሕግ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦበታል።

ፍርድ ቤቱም የዐቃቤ ሕግ ማስረጃን መርምሮ በተከሰሰበት ድንጋጌ እንዲከላከል በሰጠው ብይን ተከሳሹ 3 የመከላከያ ማስረጃ ያቀረበ ቢሆንም የዐቃቤ ሕግ ማስረጃን በተገቢው ማስተባበል ባለመቻሉ የጥፋተኝነት ፍርድ ሰጥቷል። ከዚህም በኋላ ተከሳሹ አምስት የቅጣት ማቅለያ አስተያየት አቅርቧል። በዐቃቤ ሕግ በኩል ግን የቅጣት ማክበጃ አስተያየት አልቀረበም። ፍርድ ቤቱም ተከሳሹ ያቀረበውን የቅጣት ማቅለያ አስተያየት በመያዝ ዛሬ በዋለው ችሎት ተከሳሹን በዕርከን 29 መሰረት በ10 አመት ጽኑ እስራትና በሁለት ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል።

## መልካም ሥነ-ምግባር ለውጤታማ የገቢ አሰባሰብ አይነተኛ ሚና እንዳለው ተገለፀ





በገቢዎች ሚኒስቴር የተቋማዊ ስጋት ስራ አመራር እና የሥነ-ምግባር ዳይሬክቶሬት ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለተውጣጡ አመራሮች እና ሰራተኞች በሥነ-ምግባር ላይ እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚያግዝ ስልጠና በቢሾፍቱ ከተማ ተሰጥቷል። ስልጠናው ባለፉት አምስት ወራት የተሰሩ ስራዎችን በመገምገምና የተሻለ አፈፃጸም ካስመዘገቡ ቅርንጫፎች ልምድ ለመለዋወጥ፣ ብሎም ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተጠኑ ጥናቶችን በጋራ በመወያየት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን መፍታት ላይ ያለመ መሆኑን በሚኒስቴሩ የተቋማዊ ስጋት ሥራ አመራር እና የሥነ-ምግባር ዳይሬክተር አቶ ደጀኔ ደስታ ገልጸዋል።

በስልጠናው ሰነድ አቅርበው ያወያዩት እና በተለያዩ የስራ ክፍሎች የሚታዩ ክፍተቶችን የአሰራር ስርዓት ጥናት በማድረግ መዝጋት ያስፈልጋል ያሉት በሚኒስቴሩ የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር አንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተቋማዊ ስጋት ሥራ አመራር ቡድን አስተባባሪ አቶ አማረ አለነ ሲሆኑ፥ ሰልጣኞች ጥፋት አጥፍቶ የተገኘ ሰራተኛን እንዴት መመርመር እንዳለባቸውና በጥፋቱ ልክ አስተማሪ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ እንዳለባቸው ተጨማሪ ግንዛቤ እንዲያገኙ የሚያስችል ስልጠና መሆኑን ገልፀዋል።

ሰልጣኞች በበኩላቸው ሰራተኞች ሥነ-ምግባርን በተላበሰ መልኩ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉና ከብልሹ አሰራር ራሳቸውን እንዲቆጥቡ ይህን መሰል ግንዛቤን የሚያጎለብት ስልጠና መሰጠቱ ተገቢ መሆኑን ጠቅሰው፥ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለብልሹ አሰራር ምክንያት የሚሆኑ የአሰራር ክፍተቶችን ቀድሞ እየለየ በጥናት የተደገፈ ስራ ሊሰራ እንደሚገባም አሳስብዋል።

## የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከ65 ሚሊዮን ብር በላይ የህዝብ እና የመንግስትን ሀብት ከብክነት ማዳን መቻሉን አስታወቀ



የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ መንግስቱ ላሎ እንደገለፁት ኮሚሽኑ ነጻና ገለልተኛ ሆኖ በአዋጅ የተሰጠውን ተልዕኮ በአግባቡ እየተወጣ መሆኑን ጠቁመው፥ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ በጥናትና ምርምር የተለዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማዘጋጀት ለ165 ሺህ ተሳታፊዎች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል ብለዋል። በዘርፉ የተከናወኑ ተግባራት ውጤታማነታቸውን ከማረጋገጥ ረገድም 17 ያህል ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር ስራዎችን በማካሄድ 190 ያህል ምክረ ሀሳቦችን ለየተቋማት መስጠት መቻሉን ነው ኮሚሽነሩ ያብራሩት።

በክልሉ የ33 ሺህ 856 አመራሮች የሀብት ምዝገባ ስራ መሰራቱን ገልፀው፥ የመጀመሪያ 25 አስመዝጋቢ አመራሮች ላይ በተካሄደው የሀብት ማጣራት ስራም 7 መኖሪያ ቤቶችን፣ 4 የድርጅት ቤቶችን እንዲሁም በባንክ አካውንት ወደ 682 ሺህ 775 ብር ማሳገድ መቻሉን ነው ያስታወቁት።

በሶስት ተከታታይ ዓመታትም 919 ጥቆማዎችን እና አቤቱታዎችን በመቀበል 65 ሚሊዮን 519 ሺህ 490 ብር የህዝብ እና የመንግስት ሀብት ከብክነት ከማዳን ባሻገር 99 ሺህ ካሬ የከተማ ቦታን ማሳገድ ተችሏል ብለዋል።

ተቋማት ወጥና ግልጽ የሆነ አሰራሮች ከመዘርጋት ረገድ ውስንነት መኖሩ፣ የህዝቡ ግንዛቤ እና ተሳትፎ በሚፈለግ ደረጃ አለመሆኑ፣ የፍርድ አሰጣጥ ሂደቱ ላይ ጠንከር ያለ ውሳኔ አለመሰጠቱ ለዘርፉ ስራ ውጤታማነት ማነቆ መሆናቸውን ኮሚሽነሩ ተናግረዋል። ኮሚሽኑ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ከወትሮው በበለጠ ሁኔታ ለመዋጋት የሚያስችል ቅንጅታዊ አሰራሮችን ከተቋማት ጋር ፈጥረው እየሰራ መሆኑን ገልፀው፥ ይህንኑን ለመዋጋት በሚደረገው ጥረት ሁሉም ዜጋ የድርሻውን ሊወጣ ይገባል ሲሉም አሳስበዋል።

## የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓትን በማጠናከር ብልሹ አሰራሮችን በማስወገድ ያሉንን ውስን ሀብት በቁጠባ መጠቀም ይገባል አቶ ፋጂዮ ሳፒ





የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል መንግስት ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ላይ ያተኮረ ስልጠና በሚዛን አማን ሰጥቷል። በስልጠናው መድረክ የተገኙት በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የመሠረተ ልማት ክላስተር አስተባባሪ እና የክልሉ ትራንስፖርትና መንገድ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ፋጂዮ ሳፒ የፋይናንስ አሰራር ስርዓት ጠንካራና ከብልሹ አሰራር የጸዳ ሊሆን ይገባል ብለዋል። የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓትን በማጠናከር ብልሹ አሰራሮችን በማስወገድ ያሉንን ውስን ሀብት በቁጠባ በመጠቀም የህዝቡን የመሠረተ ልማት ጥያቄዎች በተገቢው መመለስ ይገባልም ብለዋል።

የክልሉ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ ወ/ሮ ወሰነች ቶማስ በበኩላቸው ከክልሉ ምስረታ ወዲህ የመንግስት ፋይናንስ አሰራር ስርዓት ለማሻሻል መጠነ ሰፊ ስራዎች ተሰርተዋል ብለዋል። ውስን የሆነውን ሀብት በቁጠባ የመጠቀም ባህልን በማዳበር ብክነትንና ብልሹ አሰራሮችን ማረም እንደሚገባም ወ/ሮ ወሰነች ተናግረዋል። በዚህም ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለውን አሰራር ለማስፈን የተለያዩ ፕሮጀክቶች ተቀርጸው ስራ ላይ እየዋሉ እንደሆነም አመላክተዋል።

## ሙስና እና ሌብነትን ለማስወገድ የፍትህ አካላት በቅንጅት መስራት እንደሚጠበቅባቸው ተገለፀ



የህግ የበላይነትን የሚፈታተኑት ሙስና እና ሌብነትን ለማስወገድ የፍትህ አካላት በቅንጅት መስራት እንደሚጠበቅባቸው ተገልጿል። ይህ የተገለፀው የፌዴራልና የክልሎች የፍትህ አካላትበአገር አቀፍ የፍትህና የዳኝነት ሪፎርም ላይ የሚመክር የጋራ መድረክ በአዳማ በተካሄደበት ወቅት ነው።

የፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ተስፋዬ ዳባ በመድረኩ እንደገለፁት ህዝቡ በፍትህ ስርዓትና በዘርፉ ተቋማት ላይ ጠንካራ አመኔታ እንዲኖረው ትብብርና ቅንጅታዊ አሰራር መጠናከር አለበት። በተለይም የህግ የበላይነትን የሚፈታተኑት እንደ ሙስና፣ ሌብነትና ብልሹ አሰራር እንዲሁም የዜጎች የመልካም አስተዳደር ችግር ለማስወገድ የፍትህ አካላት ሚና የማይተካ መሆኑን ተናግረዋል።

በፍትህ ዘርፉ ያሉ ሙያተኞችን በሥነምግባር፣ በዕውቀትና ክህሎት ብቁ ከማድረግ አንፃር እየተከናወኑ ባሉ ስራዎች አመርቂ ውጤት እየተገኘባቸው አይደለም ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ይህም ከዘርፉ ተግዳሮቶች መካከል ተጠቃሽ ናቸው ብለዋል። የፍትህ ዘርፉ አሁንም ከዘልማድ አሰራር ያልተላቀቀ መሆኑን ገልጸው፤ በዘርፉ የሚስተዋለውን ችግር ለመፍታትም የኢትዮጵያ የፍትህ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድና ፍኖተ ካርታ ተዘጋጅቶ ወደ ተግባር መግባቱን ገልፀዋል።

## የፋይናንስ ደህንነት ብሔራዊ ኮሚቴ ባካሄደው ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ እና አቅጣጫ ማስቀመጡ ተገለፀ







የፋይናንስ ደህንነት ብሔራዊ ኮሚቴ ታህሳስ 08/2016 ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ እና አቅጣጫ አስቀምጧል።

የፋይናንስ ደህንነት ብሔራዊ ኮሚቴ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመደገፍ ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በአገር ውስጥ ያሉ ተቋማት መካከል የስራ ትብብርና ቅንጅት እንዲጠናከርና ውጤታማ እንዲሆን የተቋቋመ ነው። የብሔራዊ ኮሚቴው አባላት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራል የመንግስት ተቋማት የበላይ ኃላፊዎች የተዋቀረ ሲሆን፥ በስሩም በተለያዩ ቴክኒካል የስራ ቡድኖች የተደራጀ ነው።

ብሔራዊ ኮሚቴው ወንጀሎቹን ከመከላከልና ከመቆጣጠር ጋር በተያያዘ አገራዊ የትብብርና ቅንጅት ስራዎችን ውጤታማነት ከማሳደግ አንጻር የተዘጋጀው የውስጥ የአሰራር ስርዓት ላይ ተወያይቶ ያጸደቀ ሲሆን፥ በዚሁ መሰረት ወደ ስራ እንዲገባ ወስኗል። በሌላ በኩል ደግሞ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርትኝነትን በገንዘብ መርዳት ጋር በተያያዘ በፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ተጠንቶ በቀረበው ጥናት ላይ ተወያይቶ በሚመለከታቸው አካላት በቀጣይ መወሰድ በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ አቅጣጫ ማስቀመጡ ተገልጿል።

ኢትዮጵያ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር አዋጅ ቁጥር 780/2005 አውጥታ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ትገኛለች። አዋጁ ወንጀሎቹን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት እንደ ስራ ባህሪያቸው ሃላፊነትን ለይቶ ያስቀመጠ ሲሆን፥ በባለድርሻ አካላት መካከል የሚኖር ትብብርና ቅንጅትም የተጠናከረ እንዲሆን በግልጽ ተመላክቷል። ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌደራል የመንግስት ተቋማት የፋይናስ ደህንነት የብሔራዊ ኮሚቴው አባላት መካከል የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ይገኝበታል።

በህገ-ወጥ መንገድ ወደ ውጭ አገር ለመላክ ከግለሰቦች ገንዘብ የተቀበለችው ግለሰብ በጽኑ እስራት ተቀጣች

## በህገ-ወጥ መንገድ ወደ ውጭ አገር ለመላክ ከግለሰቦች ገንዘብ የተቀበለችው ግለሰብ በጽኑ እስራት ተቀጣች



በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ዘርፍ የተደራጁና ድንበር ተሻጋሪ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ዐቃቤ ሕግ በህገ-ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ አገር ለመላክ ገንዘብ ከግለሰቦች ተቀብለሻል ባላት ግለሰብ ላይ ክስ መስርቶባት ክርክሩ ሲካሄድ ቆይቷል። ተከሳሽ ደመቀች ማጉጂ አቤቱ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1/ እና በሰው የመነገድና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 11/1/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በዐቃቤ ሕግ ስድስት ክስ ቀርቦባታል።

ተከሳሽ ወደ ውጭ አገር ሰውን ለስራ ለመላክ ፍቃድ ሳይኖራት ቀኑ በውል ተለይቶ ባልታወቀ ከሀምሌ ወር 2013 እስከ መስከረም ወር 2014 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የተለያዩ 6 ተበዳዮችን ወደ ጆርዳን አገር ልኬ ስራ አስቀጥራችኋለሁ፣ ለዝግጅቱ እንደዚሁም ለህክምና ምርመራ ብር ትከፍላላችሁ በማለት ፓስፖርት እና ፎቶግራፍ በመቀበል፣ ከ1ኛ ተበዳይ 29 ሺህ 500 ብር፣ ከ2ኛ ተበዳይ 32 ሺህ 500 ብር፣ ከ3ኛ ተበዳይ 33 ሺህ 500 ብር፣ ከ4ኛ ተበዳይ 39 ሺህ ብር፣ ከ5ኛ ተበዳይ 25 ሺህ ብር፣ ከ6ኛ ተበዳይ 23 ሺህ ብር ተቀብላለች።

ቀጥሎም ታህሳስ 12 ቀን 2014 ዓ.ም ከምሽቱ 4፡30 ሰዓት ጆርዳን አገር ስለምትሄዱ ቦሌ አለም አቀፍ አየር ማረፊያ ቀድማችሁ መድረስ አለባችሁ ብላ በመንገር እና ከሌሎች የግል ተበዳዮች ጋር ታክሲ በማሳፈር ከምሽቱ 1፡00 ሰዓት ሲሆን ቦሌ አየር ማረፊያ ካደረሰቻቸው በኋላ ግብረ-አበሯ የሆነውና ለጊዜው በቁጥጥር ስር ያልዋለ ግለሰብ የበረራ ትኬት ይዞ እየመጣ ነው በሚል ሲጠብቁ ሳይመጣ ቀርቶ የበረራ ሰዓት አልፎ ከምሽቱ 5፡ 00 ሰዓት ሲሆን ነገ ትሄዳላችሁ አሁን አልጋ ይዘን ታድራላችሁ በማለት እየተመለሱ እያለ በጸጥታ አካላት የተያዙ በመሆኑ ተከሳሽ በፈፀመችው በህገ-ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ አገር መላክ ሙከራ ወንጀል ዐቃቤ ህግ ክስ መስርቶባት ክርክር ሲደረግ ቆይቷል።

ተከሳሽ በፌደራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 20ኛ ወንጀል ችሎት ቀርባ የተከሰሰችበት ክስ በችሎት ተነቦላት ድርጊቱን አልፈፀምኩም በማለቷ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ተከሳሽ እንድትከላከል ብይን ተሰጥቶ ተከሳሽ የመከላከያ ምስክሮችን አቅርባ ያሰማች ቢሆንም በዐቃቤ ሕግ የቀረበባትን ክስ መከላከል ባለመቻሏ ምክንያት ፍርድ ቤቱ በተከሳሿ ላይ የጥፋተኛነት ፍርድ በመስጠትና የቅጣት ውሳኔ በማሳረፍ በ14 ዓመት ጽኑ እስራት እና በ30 ሺ ብር የገንዘብ መቀጮ እንድትቀጣ እንዲሁም ከህዝባዊ መብቶቿ ለ5 ዓመት ታግዳ እንድትቆይ ሲል ተገልጿል።

## ለገቢዎች ሚኒስቴር የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አመራር እና ሰራተኞች ሥነ-ምግባር ላይ ያተኮረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መሰጠቱ ተገለፀ





ለገቢዎች ሚኒስቴር የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አመራር እና ሰራተኞች ሥነ-ምግባር ላይ ያተኮረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መሰጠቱ ተገልጿል። በመድረኩ ላይ የተገኙት የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ያሬድ ፈቃደ እንደገለፁት ሀገራችን ኢትዮጵያን በጽኑ የኢኮኖሚ መሰረት ላይ ለማቆም ተቋሙ የሚሰበስበው ገቢ ዋነኛ መሰረት መሆኑን አንስተው፥ ተግባራትን ስንሰራ በንጹህ ህሊና እና በንጹህ እጅ መሆን አለበት ሲሉ አሳስበዋል። ስልጠናው ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመቀነስ ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን፥ በአመራሩ እና በሰራተኛው አመለካከት ላይ በመስራት እና በማነቃቃት መልካም ሥነ-ምግባርን የተላበሰ አገልጋይን ማፍራት ተቋሙ መሰብሰብ ያለበትን ገቢ እንዲሰበስብ የሚያግዝ መሆኑንም አንስተዋል።

ስልጠናውን የሰጡት የብሬክስሩ ትሬዲንግ ኢ.ማ ስራ አስኪያጅ እና ማህበረሰብ አንቂ አቶ ነፃነት ዘነበ እንደገለፁት ህይወትን በአዎንታዊ መልኩ እንዴት መቀየር ይቻላል? ቀና አስተሳሰብን መገንባት፣ አገልጋይነት እና ተጽዕኖ ፈጣሪነት እንዲሁም ስኬታማ ስራ እንዴት እንስራለን? በሚሉት ሀሳቦች ላይ በማተኮር ለሚያጋጥሙን ችግሮች መፍትሄ በመስጠት ሀገርን ታማኝ ሆኖ ማገልገል እና ስኬት ላይ አተኩሮ መስራት አስፈላጊ መሆኑን አሳስበዋል።

## ኮሚሽኑ በ25 የዘርፍ ተቋማት ውስጥ ከሚሰሩ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ስራ አስፈፃሚዎች እና ባለሙያዎች ጋር የግንዛቤ መፍጠሪያ የውይይት መድረክ አካሄደ





የውይይቱ መድረኩ ዋና ዓላማ በሙስና መከላከል ዋና ዋና ተግባራት ላይ በምን መልኩ መስራት እንደሚገባ ግንዛቤ ለመስጠት ታሳቢ ያደረገ ሲሆን፣ የሙስና መረጃ ቅበላና የሀብት ምዝገባ አያያዝ፤ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራዎች እና የሙስና መከላከል ስትራቴጂ አስፈላጊነት በሚሉ የመወያያ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ መፍጠርን ታሳቢ ያደረገ መሆኑ ተገልጿል።

የሙስና መረጃ ቅበላና የሀብት ምዝገባ አያያዝ በተመለከተ የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና መረጃ አሥተዳደርና የሀብት ምዝገባ መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ፈርዳ ገመዳ ሀሳብ የሰጡ ሲሆን የሙስና ጥቆማ በሚደረግበት ወቅት ጠቋሚው አካልም ሆነ ተቋም አስፈላጊውን ጥንቃቄን ማድረግ እንደሚገባ እና በሀብት ምዝገባ ወቅትም የግለሰቦችን ሚስጥር መጠበቅ እንደሚገባ አሳስበዋል። በኮሚሽኑ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል መሪ ስራ አስፈጻሚ አቶ ገዛኸኝ ጋሻው በበኩላቸው አስቸኳይ ሙስና ማለት ሙስና ሊፍጸም ዝግጅት እየተደረገ መሆኑ ሲታወቅ ድርጊቱ ከመፈጸሙ በፊት እንዳይፈጸም ማቋረጥ ነው ብለዋል። ስልጣንን ያለ አግባብ ተጠቅሞ የሙስና ወንጀል እንዳይፈጸም ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ከመሆኑም ባሻገር የህዝብ እና የመንግስት ሃብት ከምዝበራ ማዳን እንደሚቻል አስረድተዋል።

የውይይት መድረኩ በሁሉም ዘርፎች በሙስና መከላከል ስትራቴጂ ዝግጅት ተሳትፎ ማድረግ ያላቸውን ሚና ለመለየት ከማስቻሉም በላይ በዘርፉ የሙስና መከላከል ስትራቴጂ ለማዘጋጀት ይረዳቸዋል ያሉት በኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ጥናት መሪ ስራ አስፈጻሚ አቶ ወንድይራድ ሰይፍ ናቸው። በውይይቱ መድረኩ ለተሰጡ አስተያየቶች እና ጥያቄዎች የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ እና ም/ኮሚሽነር አቶ እሸቴ አስፋው ተገኝተው ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል።

## ኮሚሽኑ በ2016 ዓ.ም አዲስ ለተመደቡ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ባለሙያዎች የመጀመሪያ ዙር የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠቱ ተገለፀ






የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ2016 ዓ.ም አዲስ ለተመደቡ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ባለሙያዎች የመጀመሪያ ዙር የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠቱ ተገልጿል። ስልጠናው ከክልል እና ከወረዳ ለተወጣጡ ለአዳዲስ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ባለሙያዎች ከታህሳስ 23-27/2016 ዓ.ም ለተከታታይ 5 ቀናት የመጀመሪያ ዙር የአሰልጣኞች ስልጠና በይርጋዓለም ከተማ ተሰጥቷል።

በስልጠናው ላይ ተገኝተው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የክልሉ የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ወ/ሮ ዘላለም ለማ እንደገለፁት ሙስና በመንግሥት ተቋማት ውስጥ ሥር የሰደደ ችግር ሆኖ መቆየቱን ጠቅሰዉ፥ በአለማችን ለሰው ልጆች ሰላምና ህይወት መጥፋት፣ ለፍትህና ፍትሃዊነት መጓደል፣ ለኢኮኖሚያዊ፣ ለማህበራዊና ለዴሞክራሲያዊ ዕድገቶች መቀጨጭ ዋና ዋና ከሚባሉ መንስኤዎች መካከል ሙስና ቀዳሚዉን ስፍራ እንደሚይዝ ተናግረዋል። ሙስና ሀገራችን ለያዘችው የልማት፣ የዴሞክራሲ፣ የመልካም አስተዳደርና ለብልጽግና ጉዞ ተግዳሮቶች ከሆኑት ዉስጥ አንዱ ነዉ ያሉት ኮሚሽነሯ፥ በዚሁ በተቀናጀ ስራ በርካታ የመንግስትና የህዝብ ሀብት የማዳን ስራ እንደተሰራም አክለዋል።

ኮሚሽነሯ አያይዘውም ቀደም ሲል የፀረ-ሙስና ትግል ለመንግስትና ለሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ብቻ የሚተዉ ጉዳይ አድርገዉ የማየት ዝንባሌዎች ትግሉ በተፈለገዉ ልክ እንዳይሄድ አድርጎት እንደቆየ ገልፀዉ፥ አሁን ግን ይህንን አመለካከት ለመቀየር የትምህርት ቤቶችንና የሲቪክ ማህበራትን በማሳተፍ በተደረገዉ ሰፊ ስራ አመርቂ ዉጤት እንደታየ አብራርተዋል። የሙስና ወንጀል የሚፈፀመዉ በሞራል ዉድቀት መሆኑን ገልፀዉ፥ ወንጀሉ በአገር ላይ እያስከተለ ያለውን ኪሳራ ለመከላከል የተደራጀ እና ንቃተ ህሊናው ከፍ ያለ ማኅበረሰብ ለመፍጠር መስራት፣ ሙስና ይፈፀማል ተብሎ በተጠረጠሩ ቦታዎች ላይ ጥናት አድርጎ የቅድመ መከላከል ስራዎችን መስራት ከሰልጣኞች የሚጠበቅ ተግባር እንደሆነ በመጥቀስ ስልጠናዉ ለዚሁ ትግል ትልቅ ግብዓት እንደሚሆንላቸዉ ገልፀዋል።

## በክልሉ የተጀመረው የሀሰተኛ ትምህርት መረጃ ማጥራት ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል

አቶ አስራት አዳሮ

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ለባለድርሻ አካላት የአቅም ግንባታ ስልጠና በቦንጋ ከተማ መስጠቱ ተገልጿል። ቢሮው ቀልጣፋ፣ ፈጣንና ተገልጋይን የሚያረካ የመንግሥት አግልግሎት ለዜጎች ለማቅረብ የሚያስችል የለውጥ አሰራሮች ባሏቸው ጉዳዮች ላይ ከክልሉ ስድስቱም ዞኖች ለተወጣጡ የዘርፉ አመራሮችና ባለሙያዎች ለሁለት ቀናት በቦንጋ ከተማ ስልጠና ሰጥቷል። ክልሉ ከተደራጀ ወዲህ የመንግሥት አግልግሎት አሰጣጥን ለተገልጋዮች ምቹና ቀልጣፋ ለማድረግ መጠነ ሰፊ ተግባራት መከናወናቸውን የገለጹት የቢሮ ኃላፊ አቶ አስራት አዳሮ፣ ከነዚህም ውስጥ በግምገማ ቀደምትነት የሚጠቀሰው ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ መነሻ የመዋቅር ማጣጣምና መልሶ ማደራጀት ስራ አንዱ መሆኑን አስረድተዋል።





በዚህም ወጪዎችን በመቀነስ የመንግሥት የአግልግሎት አሰጣጥን ዘመናዊና ቀልጣፋ የማድረግ ተግባር ተስፋ ሰጪ እንደሆነ ተናግረዋል። በቢሮክራሲ የተተበተበውን የአግልግሎት አሰጣጥ ለማዘመን ተቋማዊ የመፈጸም አቅምን ማጎልበት እንደሚገባ የገለጹት አቶ አስራት፣ በክልሉ የተጀመረው የሀሰተኛ ትምህርት መረጃ ማጥራት ስራም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል። ስልጠናው በሰው ሀብት አደረጃጀት ተግባራት፣ በኢንስፔክሽን ጥናት ሰነድ ትግበራ፣ የሰው ሀብት መረጃ አያያዝ፣ በተቋም ተኮር የለውጥ ትግበራ እንዲሁም በመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች አፈታት ላይ የሚያተኩር መሆኑን ተመላክቷል።

## በንግዱ ዘርፍ የሚስተዋለውን የሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭነት ለማስቀረት በትኩረት መሰራት እንዳለበት ተገለፀ





የአዲስ አበባ ከተማ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ በሥነምግባር፣ በሙያ ሥነምግባር እና በንግድ ሙያ ላይ የብልሹ አሰራር ተጋላጭነት ዙሪያ ስልጠና መስጠቱ ተገለፀ። የንግድ ቢሮ የከተማዋን ፋይናንስ የሚያንቀሳቅስና ትልቅ ተልዕኮ የያዘ ተቋም በመሆኑ ከሙስና እና ከብልሹ አሰራር እንዲሁም ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር የሚስተዋሉ ችግሮች ላይ በትኩረት ሊሰራ እንደሚገባ ስልጠናውን የሰጡት የኮሚሽኑ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ስልጠና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ጀንበሩ ኢርኮ ተናግረዋል። ኮሚሽኑ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ የሆኑ ተቋማትን በጥናት በመለየትና ዘርፍ ተኮር ስልጠናዎችን በመስጠት በሥነምግባር ግንባታ እና በሙስና መከላከል ላይ አተኩሮ እንደሚሰራ አቶ ጀንበሩ ገልፀዋል።

በስልጠናው የንግድ ቢሮ ከማዕከል እስከ ወረዳ ያሉ ዳይሬክተሮችና ቡድን መሪዎች የተሳተፉ ሲሆን፣ ሰልጣኞች ስለ ሥነምግባር፣ የሥነምግባር መርሆች፣ የሙስና ምንነት፣ ሙስና የሚያስከትለው ጉዳት እና የሙስና ተጋላጭነት መንስኤዎች እንዲሁም በቀጣይ መደረግ ስላለባቸው ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ስልጠና መውሰዳቸው ተገልጿል።



# ርዕሰ-አንቀፅ

## የሀገረ - መንግስት ግንባታን ለማስቀጠል በፀረ - ሙስና ትግሉ ላይ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የነቃ ተሳትፍ ማድረግ አለበት !

ሙስና ዓለምአቀፍ ችግር ነው። በተለይ በማደግ ላይ ባሉ ደሃ አገሮች ሙስና የሚያደርሰው ጉዳት በጣም ከፍተኛ ነው። በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ውስጥ የሌለውን ሀብትና ንብረት በራስ ወዳድና የሥነምግባር ዝቅጠት ባላቸው ግለሰቦች ሲሰረቅና ሲመዘበር የምስኪን ዜጎችን ኑሮ ያናጋል። ሙስና በየአካባቢው ምክንያት እየተፈለገ የዜጎች ሠላም እንዲደፈርስም ምክንያት ይሆናል። ሌባው የሰረቀውንና የመዘበረውን ሀብትና ንብረት በመጠቀም የተንደላቀቀ ኑሮ ሲኖር በላቡ ጥሮና ግሮ የሚያድረው ዜጋ ደግሞ በእነርሱ ምክንያት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ወደ ግጭትና ሠላም የሚያደፈርሱ ተግባራትን ለማከናወን ይገደዳል። በሙስና ሀብት ያካበተ ሌባ ገበያ ላይ የፍጆታ ዕቃዎችን ለመግዛት የሚያስችል አቅም ስለሚኖረው በአንድ ሌሊት ሀብት ለማካበት ከሚሯሯጠው ነጋዴ ደግሞ አጋጣሚውን በመጠቀም በገበያ የፍጆታ ዕቃ ላይ ምክንያታዊ ያልሆነ ዋጋ ጭማሪ ያደርጋል። በዚህ ምክንያት በላቡና በጥረቱ የሚኖረው ዜጋ ላይ የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት እንዲባባስ ያደርጋል። ይህ የተባበሩት የህገ-ወጦች/ሌቦች ተግባር ዜጎች የመንግስት አስተዳደር ላይ ቅሬታ እንዲኖራቸው ያደርጋል።

በሌላ መልኩ አንዴ በአቋራጭ ለመበልፀግ የሚሯሯጡና በተቋማት ውስጥ በአደራ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በመጠቀም የመንግስትን በጀት በተለያየ ዘዴ የሚመዘብሩና የሚሰርቁ ሌቦች በሀገር ላይ የሚያደርሱት የኢኮኖሚና የልማት ዕድገት እንቅፋት በይደር ንጹህ ዜጋው ከመንግስት ማግኘት የሚገባውን መሰረተ ልማቶችን እንዲያጣ ምክንያት በመሆን ዜጋው በመንግስት አስተዳደር ላይ ጥላቻ እንዲፈጠር ያደርጋል። በተቋም የሚፈጸም የሙስና ድርጊት ላይ መታገል ያለበት በመንግስት ተቋማት ውስጥ ያሉ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ሲሆኑ፣ የተቋማት ተገልጋዮችም በሚፈጸመው ሙስና ላይ የመረጃ እውቀት ስለሚኖራቸው የደረሰባቸውን፣ የሰሙትንና ያዩትን ወዲያው ማጋለጥና መታገል ይጠበቅባቸዋል።

ከሚታወቀውና ህጋዊ ገቢ ውጪ በህገ-ወጥ መንገድ ሀብት የሚያካብቱ ሰዎች በየአካባቢው ስለሚኖሩ የቤተሰብና የማህበረሰብ አባላትም ምንጩ ያልታወቀ ሀብት የሚያከብቱ ሰዎች ላይ ግንዛቤ ሲኖራቸው መረጃውን ለሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከማስተላለፍ በተጨማሪ ምንጩ የማይታወቅ ሀብት የሚያካብቱ ሰዎችን ከማህበረሰብ አባልነት ማግለል ይኖርባቸዋል።

የሙስና ትግል የሁሉም ዜጋ ትብብርና አጋርነትን የሚጠይቅ ነው። የሃይማኖት ተቋማት በየቤተክርስቲያኑና በየመስጊዱ በሚሰጡት አስተምሮት ምዕመናን አስናዋሪ ከሆነው ሙስና ራሳቸውን በማራቅ በላብና በጥረት መኖርና መክበር እንደሚቻል ማስተማር አለባቸው። ሙስና መፈጸም በምድር ላይ በህግ የሚያስጠይቅ ብቻ ሳይሆን በፈጣሪ ዘንድም የሚያስኮንን አስናዋሪ ድርጊት መሆኑን በትጋት ግንዛቤ መፍጠር ይኖርባቸዋል። የሥነምግባርና የግብረ-ገብ አስተምሮ ጥሰው ሙስና የፈጸሙ ሌቦችን ደግሞ የማውገዝ የሃማይኖት ተቋማት አንዱ ሚና ሊሆን ይገባል።

ሚዲያዎች ለማህበረሰቡ ሙስና መፈጸም በሁሉም ዘንድ አስናዋሪ ተግባር የሆነ በህግ የሚያስቀጣና የኑሮ ውድነትን የሚያመጣ፣ ቤተሰብን የሚበትን፣ የሀገርን እድገትና ልዕልና እንደካንሰር ውስጥ ውስጡን በመቦርቦር ወደ አዘቅት ጎደና የሚመራ ድርጊት መሆኑን በየጊዜው ግንዛቤ መፍጠር ይኖርባቸዋል። እንዲሁም በምርመራ ጋዜጠኝነት ሌቦች የሚፈጽሙትን ሙስና በመፈልፈልና በመመርመር የማጋለጥ ሥራን በትጋት በመሥራት የዜጎቻቸው አጋር መሆናቸውን በተግባር ማሳየት ይጠበቅባቸዋል።

በሀገራችን የተደራጁት የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶችም ህዝብ ወክለው የሚንቀሳቀሱ ከመሆናቸው አንፃር ወክለው ለሚንቀሳቀሱለት ዜጋ የበኩላቸውን ድርሻ ሊወጡ ይገባል። በሀገር ውስጥ ራስ ወዳድና በሥነምግባር የዘቀጡ ጥቂት ሌቦች የሀገርን ሀብትና ጥሪት መዝበረው የተንደላቀቀ ኑሮ ሲመሩ ብዙሃኑ ህዝብ ደግሞ የበይ ተመልካች እንዳይሆን የወከሉትን ህዝብ ሥነምግባርና ግብረገብ የማስተማርና የማስረጽ እንዲሁም የደረሰባቸውን፣ የሚያዩትንና የሚሰሙትን የሙስና ድርጊቶችን የሙስና መከላከል ሥራን ለሚያስተባብረው አካላት በመጠቆምና በማጋለጥ የዜግነት ሚናቸውን እንዲወጡ ማነሳሳትና ማነቃቃት ይገባቸዋል።

የመንግስት ተቋማት አመራሮች በሚመሯቸው ተቋማት ውስጥ የመንግስት ሀብት በሌቦች እንዳይመዘበር የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓትን ማጠናከር አለባቸው። ሌቦች ሙስና እንዲፈጽሙ ምቹ ሁኔታ ሊፈጥሩ የሚችሉ አሰራሮችንና አደረጃጀቶችን በየጊዜ ፍተሻ በማድረግ የማሻሻል እንዲሁም በተቋማት ውስጥ የሚፈጸሙ የሙስና ድርጊቶች ካሉ እንዲስተካከል ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የሥነምግባራዊ አመራር ሚናቸውን በትኩረት ሊወጡ ይገባል። እንዲሁም በሀገሪቱ በተቋማት ውስጥ የሚፈጸሙ ሙስናን ጨምሮ ህገ-ወጥ ተግባራት እንዳይፈጸሙና እንዲከላከሉ የሚያስችል የጋራ እቅድ አቅደው ለትግበራ እንዲንቀሳቀሱ የመከታተልና የመገምገም ሚና በተገቢ መንገድ እንዲወጡ የማድረግም ሥራ በተቋም የአመራር ኃላፊነት ይሆናል።

ስለሆነም በተቋም ውስጥ ሙስና እንዳይፈጸም ለመከላከል እንዲያግዝ የሥነምግባር ግንባታ ሥራዎችን በቅድሚያ የመስጠት፣ በተፈጸሙ የሙስና ችግሮች ላይ ለሌላው አስተማሪ የሆነ ቅጣት ውሳኔ እንዲጣል የማድረግና በህገ-ወጥ መንገድ የተካበተ ሀብትና ንብረት የማስመለስ ሥራ ሥልጣንና ተግባር ያላቸው ተቋማት ኃላፊነታውን ሊወጡ ይገባል። ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሙስና በዜጎች ኑሮ፣ በሀገር እድገትና ብልጽግና የሚያሳድረውን ጉዳትና ተፅዕኖ ለመከላከልና ለመቀነስ የተለያዩ የመከላከልና የመዋጋት ስትራቴጂዎችን በመንደፍ የህብረተሰብ፣ የባለድርሻ አካላትና የሚዲያ ተሳትፎዎችን በተገቢው መንገድ በመጠቀም ትግሉን የመንግስትንና የህዝብን ፍላጎት በሚያረካና አመኔታ ሊያመጣ በሚችል ደረጃ ላይ ሆነው መምራትና ማስተባበር ይጠበቅባቸዋል።


ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

**ፀረ-ሙስና**
በፌደራል
የሥነምግባር እና
የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
የሚዘጋጅ ወርሃዊ
ጋዜጣ

ስልክ 011552-77-79
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች
www.feaccdars.gov.et

**ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች**

ስልክ 011552-77-92/ 011553-38-52
ሞባይል 0935947533
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ኢ-ሜይል CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስኣፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

# ቆይታ



## የሥነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ሥራን ውጤታማ ለማድረግ በዘርፍ ተቋማት ላይ የሚገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ሚናቸው ከፍተኛ ነው

### አቶ ሀረጎት አብርሃ

**የፀረ-ሙስና** ዲጂታል ጋዜጣ የ18ኛ ዕትም እንግዳችን የፌደራል በሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ማስተባበሪያ መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሀረጎት አብርሃ ናቸው። የፀረ-ሙስና ዲጂታል ጋዜጣ ከአቶ ሀረጎት አብርሃ ያደረገችውን ቆይታ ለአንባቢያን ይዛ ቀርባለች። መልካም የንባብ ጊዜ...



**ፀረ-ሙስና ፡-** የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚ የስራ ክፍል በ25 የዘርፍ ተቋማት ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራቸው ተግባራት ምንድን ናቸው?

**አቶ ሀረጎት አብርሃ፡-** በመጀመሪያ ደረጃ የስራ ክፍሉ የሚያከናውናቸው ተግባራት ከማንሳቴ በፊት ግርታ እንዳይፈጥር 25 ዘርፎች የሚለውን ትንሽ ማብራራት ያስፈልጋል። ቀደም ሲል ኮሚሽኑ ትኩረት አድርጎ ሲሰራ የነበረው በተቋማት ተግባር ተኮር ያደረገ አሰራርን ሲከተል ነበር። ለምሳሌ ብናነሳ ኮሚሽኑ ከ2014 ዓ.ም በፊት የሥነምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል ስራዎች ማለትም የስልጠና፣ የጥናት እና የሀብት ምዝገባ እንዲሁም የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የማደራጀት እና የመከታተል ስራ ላይ ትኩረት ያደረገ እቅድ እና አቅጣጫ ( Approach ) በመከተል በተቋማት ውስጥ በተወሰኑ ተግባራት ወይም አሰራሮች ላይ ትኩረት ያደረጉ ስራዎችን ያከናውን ነበር። የሚከናወኑ ስራዎች ዘርፍ ተኮር ባለመሆናቸው እቅዶች በፌዴራል ደረጃ ተንጠልጥለው እንዲቀሩ እና የታችኛው መዋቅር ስለማያሳትፍ እንዲሁም በዘርፍ ደረጃ ከፍተኛ የመወሰን ስልጣን እና ኃላፊነት ያላቸው የፓለቲካ አመራሮች ለምሳሌ ሚኒስትሮች በሂደቱ በማስተፍ እና የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመፍታት ረገድ ዘርፉን ከሙስና በፀዳ መልኩ እንዲከናወን ከማድረግ አንፃር የነበራቸው ሚና እና ተሳትፎ በጣም አነስተኛ ነበር። በዚህ ምክንያት በየዘርፉ ያሉትን ለሙስና የሚያጋልጡ ተግባራት አሳታፊ ላይ የተመሰረተና በተደራጀ ሁኔታ ለመከላከል የሚያስችል ስርዓት አልተፈጠረም። ይህን ችግር ለመቀልበስ እና ሙስና የመከላል ስራ ከተቋማዊ አሰራር ወጥቶ ዘርፍ ተኮር ለማድረግ ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ ዘርፍ ተኮር የሙስና መከላከል አሰራሮች ተግባራዊ ለማድረግ በ22 ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ለሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራ እንዲያመች የፍርድ ቤት ተቋማት በፍርድ ቤት ዘርፍ፣ የፌዴሬሽን ምክርቤት፣ የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት እና የዲሞክራሲ ተቋማት በአንድ ላይ እንደ ምክር ቤት ዘርፍ እንዲሁም ለጠቅላይ ሚኒስቴር ፅ/ቤት ተጠሪ የሆኑት ተቋማት እንደ አስተዳደር ዘርፍ በመውሰድ በአጠቃለይ በ25 ዘርፎች ላይ ትኩረት ያደረገ የሙስና መከላከል ተግባር እየሰራን እንገኛለን። በዚህ ምክንያት በዘርፍ ደረጃ ሙስናን ለመከላከል የሚያስችል አሰቻይ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ ይገኛሉ።

ወደ ጥያቄው ስገባ እንደሚታወቀው ኮሚሽኑ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 20 ንኡስ አንቀፅ 1 እና 2 መሰረት ኮሚሽኑ በየደረጀው በሚገኙ በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት እና ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሥነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ስራን የሚያስተባብሩ እና የሚፈፅሙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ያደራጃል ወይም እንዲደራጁ ያደረጋል ይላል። ስለሆነም የሥራ ክፍላችን ዋነኛ ተግባርና ኃላፊነት ከዚህ አንቀፅ የሚመንጭ ሲሆን፥ በሁሉም መንግስት መሰሪያ ቤቶች፣ የልማት ድርጅቶች እና በተመረጡ ህዝባዊ ድርጅቶች የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በአዋጁ መሰረት እንዲደራጁና ይህን ለማስፈፀም ተብሎ ከአደረጃጀት እና አሰራር ጋር በተያያዘ በተቋማት ተግባራዊ ለማድረግ ስራ ላይ የዋሉ የአደረጃጀት እና አሰራር ስታንዳርዶች አሉ። እነዚህ ስታንዳርዶች በአግባቡ ተግባራዊ መሆናቸውን የመከታተል፣ አዋጁን መሰረት አድርገው ለሚመደቡ ተቋማት በስራቸው ውጤታማ ሊያደርጋቸው የሚችል በአሰራር እና ክህሎት ላይ ትኩረት ያደረገ የዓቅም ግንባታ ስልጠና እንዲያገኙ የማመቻቸት፣ ኮሚሽኑ በየጊዜው በሚያስቀምጣቸው አቅጣጫዎች እና አንድ እቅድ አንድ ሪፓርት አሰራር መሰረት አድርገው የሚወርዱ ዘርፍ ተኮር የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል እቅዶች በአግባቡ እየተፈፀሙ ስለመሆናቸው በሱፐርቪዥን ጭምር መከታተል፣ መገምገም እና የተሻለ እንቅስቃሴ ያላቸውን እውቅና እንዲሰጣቸው የማመቻቸት፣ ከአደረጃጀት እና አሰራር አንፃር የሚያጋጥሙ ችግሮችን እንዲፈቱ ከሚመለከታቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና ተቋማት ጋር በቅንጅት መስራት ነው። በአጠቃላይ የስራ ክፍላችን ዋነኛ ተልእኮ በ25 ዘርፎች ውሰጥ ለሚከናወኑ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራዎች አሰቻይ ሁኔታ በመፍጠር ሂደት ብቁና ውጤታማ የሆነ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል አደረጃጀት እና አሰራር በተቋም ውስጥ እንዲፈጠር ማድረግ ነው።

**ፀረ-ሙስና ፡-** ኮሚሽኑ በ25 የዘርፍ ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ጋር ያለው የስራ ግንኙነት ምን ይመስላል?

# ቆይታ



ሁሉም የዘርፍ ተቋማት የተሟላ አደረጃጀትና የሠው ኃይል አላቸው?

**አቶ ሀረጎት አብርሃ፡-** ኮሚሽኑ ከሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ጋር ያለው ግንኙነት አዋጅ 1236 መሰረት ያደረገ ነው። በአዋጁ መሰረት እነዚህ የስራ ክፍሎች ከኮሚሽኑ ጋር ቀጥታ ግንኙት አላቸው። በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራ ላይ ኮሚሽኑ በሚያዘጋጀው አንድ እቅድ አንድ ሪፖርት አሰራር መሰረት በቅንጅት እየሰሩ ያሉ ናቸው። በተፈጠረው ቅንጅት መሰረት በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ላይ ዘርፍ ተኮር ስልጠና፣ ጥናት፣ አደረጃጀት እና ፎረም ላይ ውጤታማ ስራ እንዲከናወን ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው።

መንግስት በሀገር ደረጃ የሰው ሀብት ልማት እና አሰራር ለማዘመን ብሎ ከሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ሰው ሀብት አስተዳዳር ጋር በተያያዘ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያወረደው ሰርኩላር አለ። ይህ ሰርኩላር አስተዳዳራዊ ጉዳዮች እንዲያሳልጥ እሳቤ ያለው ቢሆንም በተግባር ግን ከአንዳንድ ተቋማት በሚኖረው የስራ ግንኙነት ላይ ተፅእኖ ፈጥሯል። አንዳንድ ተቋማት ሰርኩላሩን እንደ አጋጣሚ በመጠቀም በአዋጁ ላይ ከሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አደረጃጀት፣ አሰራር እና ግንኙት ጋር በተያያዘ የተቀመጡ ድንጋጌዎች የሚጣሱበትና ከኮሚሽኑ ጋር ለመተባበር የሚያቅማሙ አልጠፉም። ሆኖም ግን ኮሚሽኑ በሚከተለው ዘርፍ ተኮር አሰራር መሰረት ከሚመለከታቸው የዘርፍ አመራሮች ጋር በመነጋገር ችግሩ ለመፍታት ጥረት ይደረጋል።

አሁን ባለው መረጃ መሰረት በ25 ዘርፎች በ308 የፌዴራል ተቋማት ውስጥ ወደ 1,070 የሚጠጉ የሥነምግባር መከታተያ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ተመድበው እየሰሩ ይገኛሉ። ከ308 ተቋማት ውስጥ ከ15 የማይበልጡ የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ የልማት ድርጅቶች እና ህዝባዊ ድርጅቶች ላይ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የሌላቸው ሲሆን፥ በነዚህ ተቋማት በውስጥ አደረጃጀት ጥናት መከለስ፣ ምደባ መዘግየት ወይም ሙሉ ለሙሉ መከታተያ ክፍሎች የለቀቁባቸው ተቋማት ናቸው። ሆኖም ግን ከሚመለከታው የመንግስት አካላት እና ቦርድ አባላት ጋር በመነጋገር መልሰው እንዲያደራጁ ወይም እንዲመድቡ ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል። በሱፐርቪዥን ታግዘን በአብዛኛዎቹ ተቋማት ሟሟላት የሚገባቸውን የሰው ኃይል ያሟሉ ሲሆን፥ የተጓደሉትን በየጊዜው ክትትል እየተደረገ እንዲያሟሉ ይደረጋል።

**ፀረ-ሙስና፡-** ከ25 የዘርፍ ተቋማት መካከል በ2016 በጀት ዓመት የ1ኛ ሩብ ዓመት የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው ተቋማት እነማን ናቸው?

**አቶ ሀረጎት አብርሃ፡-** እንደሚታወቀው በ1ኛው ሩብ ዓመት ኮሚሽኑ ትኩረት አድርጎ ሲንቀሳቀስ የነበረው ሁሉንም ዘርፎች የሚያሳትፍ አንድ እቅድ አንድ ሪፖርት አሰራር ለመዘርጋት እና በእሱ ላይ ተመሰርቶ እቅድ ማዘጋጀት፥ ከኮሚሽኑ የስራ ክፍሎች ቅንጅት መፍጠር እና የጋራ እቅድ ማዘጋጀት፣ በኮሚሽኑ የ2016 በጀት ዓመት እቅድ እና ዋና አቅጣጫዎች ላይ ኦሬንቴሽን በመስጠት ወደ ስራ የማስገባት ስራ ተሰርቷል። ስለሆነም ኮሚሽኑ እና ዘርፎች በ1ኛው ሩብ ዓመት በእቅድ ዝግጅት ላይ ነበሩ ብሎ መውሰድ የሚቻል ቢሆንም በ1ኛው ሩብ ዓመት ጤና፣ ገቢዎች እና ስራና ክህሎት ዘርፍ ተኮር የአመራር ስልጠና በማዘጋጀት የተሻለ እንቅስቃሴ ያደረጉ ሲሆን፥ በ2016 በጀት ዓመት የትራንስፓርትና ሎጂስቲክስ፣ ከተማና መሰረተ ልማት፣ ግብርና፣ ፍርድቤቶች፣ ባህልና ስፓርት፣ ፍትህ እና መስኖና ቆላማ አከባቢ ዘርፎች በ1ኛ እና 2ኛ ሩብ ዓመት አዲስ ፎረም ያደራጁ ዘርፎች ናቸው።




በሶስተኛው ሩብ ዓመት በስልጠና፣ በሀብት ምዝገባ እና ፎረም እንቅስቃሴ ላይ ሁሉም ዘርፎች የተሻለ እንቅስቃሴ እና ጥረት ያደርጋሉ ብለን እናስባለን።

**ፀረ-ሙስና ፡-** በሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የማስተባበር ሥራ ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች ምንድ ናቸው? መፍትሄውስ ምንድን ነው?

**አቶ ሀረጎት አብርሃ፡-** በየዘርፉ ያሉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የማስተበባር ስራ ውጤታማ ሆኖ እንዲወጣ ከተፈለገ በዚህ ረገድ ቀጥታ ኃላፊነት እና ድርሻ ያላቸው አካላት ትብብር፣ ቅንጅትና ድጋፍ ይፈልጋል። እነዚህ የስራ ክፍሎች ተቋማት በሥነምግባር የተገነባ አገልግሎት እንዲሰጡ እና ከሙስና የፀዳ ስርዓት እንዲዘረጋ የተቋሙ ኃላፊ በሙስና መከላከል ስራ ላይ የሚያማክሩና ድጋፍ የሚሰጡ ናቸው። ኮሚሽናችን ለሚያከናውነው የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራ ላይ እጅና ጓንት በመሆን መረጃ ከማመንጨት ጨምሮ ለአጠቃላይ የሙስና መከላከል ስራ ውጤታማነት ከፍተኛ ሚና አላቸው ብለን እናምናለን።

እነዚህ ክፍሎች ይህንን ሚናቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ከተቋማት ጋር በመተባበር ለመደገፍ ጥረት እያደረገን ቢሆን፥ የተለያዩ ተግዳረቶች እና ክፍተቶች ማጋጠማቸው አልቀረም። አንደኛና ዋነኛው ምክኒያት አንድ አንድ የተቋማት ኃላፊዎች ለሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የሚሰጡት ድጋፍና እገዛ በሚፈለገው ደረጃ አለመሆን ነው። የስራ ክፍሉ ውጤታማ እንዳይሆን ተልእኮ እንደላቸው በሚመስል መልኩ የሚደረጉ ሙከራዎች አሉ። ለዚህም እንደማሳያ አድርገን የምናስቀምጣቸው የኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅና ይህን ለማስፈፀም የወጡ ስታንዳርዶች መሰረት አድርጎ ለመስራት ቁርጠኝነት ማነስ፣ በዚህም ዝቅ ያለ አደረጃጀት መዘርጋት፣ የሰው ሀይል በተሟላ ሁኔታ ያለመመደብ፣ በዩንቨርስቲዎች አከባቢ ተደጋጋሚ የአደረጃጀት እና ምደባ ስርዓት ጋር መለዋወጥ ምክኒያት በበቂ ሁኔታ ለመደገፍ አስቸጋሪ መሆኑ፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያወረደውን ሰርኩላር አጣምሞ በመተርጎም አዋጁን እና ኮሚሽኑ ያወረዳውን አቅጣጫ በአግባቡ ያለመተግበር፥ እንደሀገር ያለን ችግር የሚታወቅ ቢሆንም ለሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ግብዓት የሚሆኑት እንደ በጀትና ቁሳቁስ ያሉትን በበቂ ሁኔታ አለሟሟላት፥ መከታተያ ክፍሎች ለተቋሙ ኃላፊ የሚያቀርቡት ጥያቄዎች እና ምክረ ሀሳቦችን ተቀብሎ ፈጣን ምላሽ ያለመስጠት፥ በተቋሙ ብቁ እና ክህሎት ያለው የሥነምግባር መከታተያ ባለሙያ አለመመደብ፥ የተመደበውን ባለሙያ አለግባብ ማንሳት ወይም ዝቅ ማድረግ፥ የሚገባውን ጥቅማጥቅም አለመስጠት፥ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ከውስጥ የህግ አገልግሎት፣ ኦዲት እና ለውጥ የስራ ክፍሎች ተቀናጅተው እንዲሰሩ ከመደገፍ አንፃር ውስንነቶች መኖሩም ተጠቃሽ ነው።

ከሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችም ያሉ ተግዳሮቶች ስናይም ቀላል አይደሉም። አንድ አንድ መከታተያ ክፍሎች የተሰጣቸውን ተልእኮ በአግባቡ ተረድቶ ያለመስራት፣ ስራውን ለማከናወን እውቀትና ክህሎት ማነስ፣ ተቋሙ ውስጥ ካሉ አመራሮች እና የማነጅመንት አባላት እንዲሁም ከኮሚሽኑ የስራ ክፍሎች ጋር ያለውን የመረጃ ልውውጥ እና በቅንጅት ከመስራት አንፃር ክፍተቶች ይስተዋላሉ። በኮሚሽናችን በኩል የሚጠበቅብን ድጋፍና እና እገዛ ለማድረግ የሰው ሀይል፣ የእውቀት፣ ክህሎት እና ተግባቦት ማነስ ችግር አለ፤ ሙያ ተኮር የሆኑ ተከታታይነት ያላቸው የዓቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት የበጀት እጥረቶች አሉብን። ወቅታዊ መረጃ ላይ ተመስርቶ ግብረ መልስ ከመስጠት አንፃርም በስራ ክፍሎች ክፍተት ሊኖር ይችላል።

በአጠቃላይ የሚያጋጥሙን ተግዳረቶች እና ክፍተቶች ለመፍታት ኮሚሽናችን ከሚመለከታቸው ሚኒስቴር መሰሪያ ቤቶች፣ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እና በትብብር በመስራት ችግሮች ለመፍታት ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው፤ በዚህ ረገድም ለውጦች እየተመዘገቡ ነው ብየ አስባለሁ።

**ፀረ-ሙስና፡-** በተቋማት ላይ የክትትል እና ድጋፍ ተግባራትን እየሰራችሁ መሆኑ ይታወቃል። ድጋፍና ክትትሉ ምን ላይ

# ቆይታ





ያተኮረ ነው? ተቋማቱ እነማን ናቸው? የድጋፍና ክትትሉ ዓላማ እና የሚጠበቀው ውጤት ምንድን ነው?

**አቶ ሀረጎት አብርሃ:-** ከላይ እንደገለፅኩት የስራ ክፍላችን ከተሰጡት ተልእኮዎች አንዱ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በአግባቡ ስራ ላይ ስለመሆናቸው መከታተል፣ መደገፍ እና መገምገም ነው። የድጋፍ እና ክትትሉ ዋና ዓላማም ብቁ እና ውጤታማ የሆኑ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በየተቋማቱ እንዲደራጁ በማድረግ ኮሚሽኑ ለሚያካሂደው የፀረ-ሙስና ትግል የተመቻቸ ወይም አሰቻይ ሁኔታ መፍጠር ነው። ይህን እውን እንዲሆን ለማድረግ ከአደረጃጀት፣ አሰራር እና ከማስፈፀም አንፃር የሚያጋጥማቸው ችግሮችን በመለየት መፍታት ነው። በዚህ መሰረት በበጀት ዓመቱ 1ኛ እና 2ኛ ሩብ ዓመት ትኩረት አድርገን ወደ ስራ የገባነው በ25 ዘርፎች ውስጥ ከአደረጃጀት፣ ከአሰራር እና ከግንኙነት አንፃር ጎላ ያለ የመልካም አስተዳደር ችግር ያላቸውን 105 ተቋማት በመለየት እና ይህን ችግር ለመፍታት የሚያስችል እቅድ በማዘጋጀት ወደ ስራ ገብተናል። በሁለት ዙር ከ70 ተቋማት በላይ የመስክ ሱፐርቪዥን ማካሄድ የተቻለ ሲሆን፥ በተካሄደው ሱፐርቪዥን ጥሩ ልምድ የተገኘ ከመሆኑም ባሻገር ዘርፎችን ለማጠናከር ትልቅ እገዛ የፈጠረ ነው።

ተቋማት የሚስተዋልባቸው የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት ዝግጁ መሆናቸው እና ከሞላ ጎደል የሁሉም ተቋማት ኃላፊዎች ችግሮችን ለመፍታት ቁርጠኛ አቋም ያላቸው መሆኑን ከተደረገው ሱፐርቪዥን ግንዛቤ ተወስዷል። ይህም ኮሚሽኑ በቀጣይ ለሚያከናውነው ስራ ትልቅ ግብዓት ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን፥ የክትትልና ድጋፉ ስርዓቱን በመመሪያ በማስደገፍና በማጠናከር ጠንካራ እና ደካማ ዘርፎችን የመለየት እና ደረጃ የማውጣት ስራ በቀጣይ ተጠናክሮ የሚከናወን ይሆናል።

**ፀረ-ሙስና:-** ኮሚሽኑ በ20ኛው ዓለምአቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን ማጠቃለያ ፕሮግራም ላይ ከ25 የዘርፍ ተቋማት የተሻለ አፈፃፀም ያላቸውን ተቋማ በደረጃ የማበረታቻ ሽልማት መስጠቱ ይታወቃል። በምን አግባብ እንደተሸለሙ የሰሩትን ተግባራት በማሳያነት በመጥቀስ ከ1-3 ደረጃ የወጡ ተቋማትን ቢገልፁልን?

**አቶ ሀረጎት አብርሃ:-** የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራ የሙስና ድርጊቶችን ወይም ሙስና የፈፀሙ ሰዎችን በመኮነን ብቻ መታገል አይቻልም። በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ላይ ጥሩ ስራ የሰሩ ወይም አርዓያ ሆነው የተገኙ ተቋማት እና ግለሰቦችን እውቅና መስጠት፥ ሌሎችም በተመሳሳይ በጎ ተግባር እና አስተሳሰብ ላይ እንዲሰማሩ እና የፀረ-ሙስና ትግሉ ተዋናይ ዜጋ ለማብዛት ያግዛል፤ ይህም አዋጇችን ይደግፋል። ኮሚሽኑ የዘንድሮውን 20ኛ ዓለምአቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን ምክንያት በማድረግ ህዳር 27/ 2016 ዓ.ም በስካይላይት ሆቴል በተዘጋጀው የማጠቃለያ ፕሮግራም ላይ በ2015 በጀት ዓመት በተሻለ ሁኔታ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራን ያከናወኑ ዘርፎች፣ ተቋማት እና ግለሰቦች እውቅና ሰጥቷል።ኮሚሽኑ ለዘርፎች ወይም ተቋማት እውቅና የሰጠው ከሙስና የፀዱ ወይም ሙስና ያጠፉ በሚል እሳቤ አይደለም።

ኮሚሽኑ በበጀት ዓመቱ ያስቀመጠውን አቅጣጫ እና የራሳቸውን ተነሳሽነት እና ፈጠራ ጨምረው ከሌሎች ሲወዳደሩ የተሻለ እንቅስቃሴ ያደረጉትን እና በቀጣይ ይህን አጠናክረው እንዲሄዱ ለማበረታታት ያለመ እውቅና ነው። ከዚህ አንፃር እውቅና መሰጡ ጥሩ እንጂ ክፋት የለውም። ዘርፎችም በተመሳሳይ ሁኔታ ከአንድ እስከ ሦስት የወጡትን ጨምሮ እንደየደረጃቸው እውቅና የተሰጣቸው በ2015 በጀት ዓመት የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራ ለማከናወን በየዘርፋቸው ምን ያህል አስቻይ ሁኔታ ፈጥረዋል፤ በተፈጠረው አስቻይ ሁኔታ ምን ያህል እንቅስቃሴ አድርገዋል በሚል ነው። በዚህ መሰረት ገቢዎችና ጉምሩክ ዘርፍ፣ ኢንዱስትሪ፣ መከላከያ እና ጤና ዘርፎች እንደ ቅደም ተከተላቸው ብቁ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አደረጃጀት እና የተሟላ የሰው ኃይል በሁሉም የዘርፉ ተቋማት ወይም ተጠሪ ተቋሞቻቸው እንዲኖር በማድረግ የጎላ እንቅስቃሴ በማድረጋቸው ነው ደረጃው የተሰጣቸው። ይህን እውቅና ለመስጠት ኮሚቴ ተቋቁሞ የተሰራ ሲሆን፥ ሁሉም ዘርፎች በተዘጋጀው መስፈርት መረጃዎችን በማደራጀት እና በመተንተን ግልፅ በሆነ ሁኔታ የተከናወነ ነው። እንዲህ አይነት ተግባር በቀጣይ ዓመትም ተጠናክሮ እና ስርዓት ላይ ተመስርቶ እንዲከናወን ኮሚሽኑ እንደ አቅጣጫ አስቀምጦ እየሰራበት ያለ ጉዳይ ነው።

**ፀረ-ሙስና:-** የኮሚሽኑ የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚ መሪ ሥራ አስፈፃሚ እንደመሆንዎ መጠን የዘርፉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ዳይሬክተሮች እና ባለሙያዎች የተሰጣቸውን የሥነምግባር ግንባታ፣ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተልእኮ ከማሳካት አንፃር ሊኖራቸው የሚገባ ሥነምግባር ምንድን ነው ይላሉ? ከዚህ አንፃር ጎልቶ የታየ ችግር አለ?

**አቶ ሀረጎት አብርሃ:-** በየዘርፉ ያሉትን የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራ ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲፈፀም የጎላ አስተዋጽኦ ያላቸው አካላት ናቸው። በየዘርፉ የሚደረጉ የፀረ-ሙስና ስራዎች የማስተባበር፣ የማቀናጀት እና የመምራት ኃላፊነት አለባቸው። እነዚህ ኃላፊነቶች በአግባቡ እንዲወጡ ራሳቸው በእውቀት፣ በክህሎት እና በሥነምግባር የታነፁ መሆን አለባቸው። ከማንኛውም አመራር እና ሰራተኛ በላይ አርዓያ ሆነው መገኘት አለባቸው። እስከአሁን ካደረግነው ክትትል እና ድጋፍ አንፃር ከዓቅም እና ክህሎት ክፍተት ውጪ የጎላ የሥነምግባር ችግር ያለባቸው መከታተያ ክፍሎች አላጋጠመንም። ሆኖም ግን የሚመጡ ማንኛውም ቅሬታዎች እና ጥቆማዎች ችላ ሳንል በማጣራት እና የሱፐርቪዥን ስራ በማከናወን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ እናደርጋለን፤ በቀጣይም ችግሮች እንዳይከሰቱ እንከታተላለን።

**ፀረ-ሙስና :-** በመጨረሻም ማስተላለፍ የሚፈልጉት የቀረ ሀሳብ ካለዎ?

**አቶ ሀረጎት አብርሃ:-** በመጨረሻም ማስተላለፍ የምፈልገው መልእክት የፀረ-ሙስና ትግል የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ትብብር እና ቅንጅት የሚጠይቅ ስራ ነው። የኮሚሽኑ ሚና በዋናነት ማስተባባር ላይ የተመሰረቱ በመሆኑ የተቋማት አመራሮች ጨምሮ ሁሉም የፀረ-ሙስና ትግሉ ተዋናዮች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ሊወጡ ይገባል እላለሁ። አመሰግናለሁ!

# ሳይቃጠል በቅጠል

## በኮንስትራክሽኑ ዘርፉ የሚስተዋሉ የሙስና እና ብልሹ አሰራር ችግሮች በመበራከታቸው ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል!

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በልማት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ልዩ ሚና ያለው ኢንዱስትሪ መሆኑ ይታወቃል። ኮንስትራክሽን የማይገባበት የልማት ዘርፍ የለም ማለትም ይቻላል።

እንደ መንገድ፣ የባቡር መስመር፣ የቤቶች ልማት ፕሮጀክቶቻችን ላይ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የተጫወተውና እየተጫወተ የሚገኘው ሚና ለዚህ ቅርብና ግልጽ ማሳያ ነው። እንደ ትምህርት ቤቶች፣ የሕክምና ተቋማት፣ ዩኒቨርስቲዎቻችን እና ሌሎች የማኅበራዊ መሠረተ ልማት ተቋሞቻችን ላይ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የነበረውንና ያለውን ሚናም እዚህ ጋር ማስታወስ ተገቢ ነው። በአጠቃላይ በየትኛውም የኢኮኖሚ ዘርፍ ፈጣን ዕድገት ለማምጣት ቀልጣፋና ጠንካራ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መገንባት ያስፈልጋል ማለት ነው።

የሀገራችን ሕዝብና መንግሥት ዋነኛ የልማት አጀንዳ የረዥም ጊዜ መገለጫዋ የሆነውን ድህነት ታሪክ ማድረግ ነው። ድህነት በራሱ እልፍ መገለጫዎች ያሉት ሲሆን፥ በዋነኛነት ግን ቃሉ በማኅበረሰብ ውስጥ በሚኖር ኢ-ኢፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል አማካኝነት ዜጎች መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ማሟላት ሳይችሉ ሲቀሩ ነው የሚለው ገዥ ትርጓሜ ነው።

የሀገራችን ሕዝብና መንግሥት ዋነኛ የልማት አጀንዳ የረዥም ጊዜ መገለጫዋ የሆነውን ድህነት ታሪክ ማድረግ ነው። ድህነት በራሱ እልፍ መገለጫዎች ያሉት ሲሆን፥ በዋነኛነት ግን ቃሉ በማኅበረሰብ ውስጥ በሚኖር ኢ-ኢፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል አማካኝነት ዜጎች መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ማሟላት ሳይችሉ ሲቀሩ ነው የሚለው ገዥ ትርጓሜ ነው።

ኢትዮጵያ ለዓመታት በተለያዩ መሥፈርቶች ድሀ በመባል ከተፈረጁ ሀገራት ቀዳሚ ሆና ቆይታለች። ዜጎቿ ዕጣ ፈንታቸው ሳይሆን በተለያዩ የመልካም አስተዳደር፣ የዴሞክራሲና የልማት እጦት ምክንያት የድህነት ገፈቱን ቀምሰዋል። ከዛሬ ሁለት አስርት ዓመታት ጀምሮ የሀገር ገፅታና የዜጎች የተጎሳቆለ ኑሮ ከሥር መሠረቱ ለመለወጥ የተጀመረው ዘመቻ የማታ ማታ ተጨባጭና አመርቂ ውጤቶችን በማስመዝገብ እነሆ አሁን እውነትም ድህነትን ታሪክ ማድረግ የሚቻልበት ወቅት ላይ እየደረስን መሆኑን የሚያመለክቱ ፍንጮች እየታዩ ነው። በተለይም የልማት ክፍሎችንና ኅብረተሰቡን ቀዳሚ ተሰላፊ በማድረግ በተለያዩ ጊዜያት ተዘጋጅተው እውን በሆኑ እቅዶች አማካኝነት የተሠሩ በርካታ የመልካም አስተዳደርና የልማት ሥራዎች የዜጎችን ጥቅም መሰረት ያደረገ አስደናቂ እድገት እንድናስመዘግብ አስችሎናል።

በዕቅዱ መሠረት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ከተሞች ለዘላቂና ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ልማት የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲጫወቱ በሚያስችል አቅጣጫ የተቀመጡትን ዕቅዶች ተረክቦ ለተፈጻሚነቱም መትጋት ከጀመረ ሰነባብቷል።

የከተማ ነዋሪዎችን የመጠለያ እጦት ከማቃለል ጀምሮ የትምህርት የጤና የኢንዱስትሪውን ልማት እውን የሚያደርጉ የተለያዩ ግዙፍ የልማት ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ማድረግ በኮንስትራክሽን ዘርፍ ከተጣሉ ግቦች መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ናቸው። በተለይም የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችን የቤት ባለቤት ለማድረግ በተያዘው ሰፊ እቅድ ላይ የኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ መሆኑም ይታወቃል። ታዲያ ድህነትን የማስወገድና




ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልን ማስፈን የሁሉም ዘርፍ ግብ ከሆነ ዘንዳና በተለይም የኮንስትራክሽን እንዱስትሪው በዚህ ላይ ያለው ሚና የላቀ ከሆነ የድህነት ምንጭና የልማት ነቀርሳ የሆነው ሙስና በዚህ ዘርፍ ውስጥ ያለውን ልዕልና ማወቅና ትኩረት መስጠት ተገቢ ስለሚሆን በዘርፉ ከሚከናወኑ የሙስና አሻጥሮች መካከል ጥቂቶቹንና ዋና ዋና የሆኑትን መጠቆም እየተደረገ ባለው የፀረ-ሙስና ዘመቻ ላይ አስተዋጽኦ የማድረግ የዜግነት ግዴታ መወጣት ከመሆኑም በላይ ሌሎችም ለኮሚሽኑ መረጃ በመስጠት ያግዙ ዘንድ የመነሻ ግብአት ይሆናቸዋል።

የፀረ-ሙስና ትግሉ በኮንስትራክሽን ዘርፉም እንደሚቀጥል በማውሳት ትኩረት ያሻቸዋል ከሚባሉ ነጥቦች መካከል ከቅድመ ግንባታ የሚጀምረው የጥራት ችግር ነው። ፕሮጀክቶች ሲጠኑ አሊያም ዲዛይናቸው ሲዘጋጅ በቂ እውቀትና ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች ካልታዘጋጁ የተፈለገውን ውጤት ማምጣት ስለማይቻል ሥራውን እንዲቆጣጠሩ የሚሰየሙ አማካሪ መሐንዲሶች ጥራቱን ለማስጠበቅ የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት አለባቸው። እዚህ ላይ ግልጽ መሆንና መብራራት ያለባቸው ጉዳዮችም አሉ። ለምን ቢባል ከላይ እንደተመላከተው በፀረ-ሙስና ትግሉ ላይ ሁሉም ዜጋ የድርሻውን እንዲወጣ ነው። ይኸውም ከቅድመ ግንባታ ይጀምራል የተባለው የጥራት ችግር በቂ እውቀትና ልምድ ከሌላቸው ባለሙያዎች ጋር መያያዙን ነው መብራራትና ግልጽ መሆን አለበት የሚባለው። ቅድመ ግንባታ ማለት የሚጀምረው ከፕሮጀክት ዝግጅቱ ሲሆን እስከ ጨረታ ያለውን ሂደት የሚያጠቃልል ነው።

በዚሁ መሠረት በቅድመ ግንባታ ወቅት በጨረታ አዘጋጁ (አማካሪ ድርጅቱ) በሥራ ተቋራጩና በተቆጣጣሪ መሀንዲሱ መካከል ያለው የጥቅም ግንኙነት የሚጀምረው ከፕሮጀክቱ ዝግጅት ነው። የግንባታ ዲዛይኑን የሚያዘጋጀው አማካሪ ድርጅት ሥራውን አጠናቆ ጨረታውን ለሚያሰናዳው ወይም Bill of quantity specification ለሚያዘጋጀው quantity surveyer ይሰጠዋል። ይህ ባለሙያ በዕውቀት እና በልምድ ችግር ሳይሆን ከሥራ ተቋራጩ ጋር በመሠረተው የጥቅም ግንኙነት የግንባታ ሥራውን ጥራትና የመንግሥትን ሀብት ለድርድር ያቀርበዋል። የሙስና ስልቱን የሚጀምረውም ከመሠረተ ቁፋሮው ነው። እንደሚያሸንፍ ከሚጠበቀው እጩ ሥራ ተቋራጭ ጋር በመመሳጠር በትክክለኛው አግባብ ለምሳሌ የመሠረት መጣያ ቁፋሮው ጥልቀት 1 ሜትር ቢሆን ጨረታ አዘጋጅ የሆነው ባለሙያ 2 ሜትር አድርጎ በጨረታ ሰነዱ ላይ ያዘጋጀዋል።

ይህ ደግሞ የጠቅላላ ግንባታውን በጀት ከፍ የሚያደርገው እና ከትክክለኛው ዲዛይን

# ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሁሉም ህብረተሰብ ክፍል የነቃ ተሳትፎ ያስፈልጋል!



ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ባሻገር ያለው የአንድ ሜትር ልዩነቱን ዋጋ ተሞዳማጆቹ ኪስ ይገባል ማለት ነው። በተለይም የመሠረት ግንባታ ከመሬት በታች ያለ ጉዳይ በመሆኑና ተቆጣጣሪ መሀንዲሱና ሥራ ተቋራጩ በሙስና እስከተጣመሩ ድረስ በርክክብ ጊዜም ቢሆን የማይታይ በመሆኑ ችግሩ ሊከሰት የሚችለው ከጥቂት ዓመታት በኋላ በመሆኑ የሕዝብ ሀብት ምን ያህል በጥቂቶች ጥቅመኝነት ለብክነት እንደሚዳረግ የሚያመላክት ሂደት ነው።

በኮንስትራክሽን ጨረታ ሕግ መሠረት under estimation (ከጠቅላላ ዋጋ በታች) እና over estimation (ከጠቅላላ ዋጋ በላይ) የሚባሉ ነገሮች አሉ። ምን ማለትስ ናቸው? ለምትሉ ቀደም ተብሎ በተጠቀሰው አማካሪ ድርጅት ውስጥ ያለው ጨረታ አሰናጁ ባለሙያ 4 አጠቃላይ የግንባታውን ወጪ (Engineering estimation) ያዘጋጃል። ይህ ዋጋ ለማንም የማይገለጽና በጨረታው ተወዳዳሪዎች ከተሞላው ዋጋ 10 በመቶ ዝቅ ያለው under estimarion በመሆን ከ10 በመቶ ከፍ አድርጎ ዋጋ ያቀረበው ደግሞ over estimation ሆኖ ከጨረታው ውጪ ሲሆን በጨረታ አሰናጁ ለተዘጋጀው ጠቅላላ ዋጋ (Engineering estimation) የቀረበና ከ10 በመቶ ዝቅ ያላለው አካል የጨረታው አሸናፊ ይሆናል ማለት ነው።

ከላይ በተጠቀሰው የሙስና ስልት መሠረትም እንኳንስ ጠቅላላ የሆነውን የግንባታ ወጪ ይቅርና ጨረታውን በአጠቃላይ በጋራ በማለት በሚቻል ደረጃ ከባለሙያው ጋር ያዘጋጀው የሥራ ተቋራጭ አሸናፊ ሆኖ እንደሚወጣ ምንም ጥርጥር አይኖረውም። ከዚያ በኋላ ያለውና ከጠጠር፣ ከሲሚንቶ፣ ከብረትና ሌሎች ግብዓቶች ጋር በተያያዘ የሚሠራው አሻጥር ደግሞ በተቋራጩ በተቆጣጣሪው አካል ብቻ የሚፈፀም ይሆናል ማለት ነው።

ተቆጣጣሪ መሀንዲሱ በተሰጠው ኀላፊነትና ተግባር መሠረት ለፕሮጀክቱ የሚውሉ የጠጠር ዓይነቶች Material test መደረጋቸውንና ማለፋቸውን የማረጋገጥ ትክክለኛ የሳጥን (መሥፈሪያ) መጠንና የድብልቅ ምጣኔ የብረት ደረጃና መጠን ሳይጠበቅ ሥራ ተቋራጩ በሥራ ጊዜ ለጥራቱ ሲባል እንዲፈርስ ማድረግ አለበት። ሆኖም እስከዛሬ ቢያንስ ይህ ሕንፃ ወይም ይህ መንገድ ደረጃውን በጠበቀ ግብአት ባለመሠራቱ እንዲፈርስ ተደረገ ሲባል ብዙ ጊዜ በሚባል ደረጃ ሰምተን አለማወቃችን የተቆጣጣሪውን እና የሥራ ተቋራጩ የጥቅም ትስስር ምን ያህል ስር የሰደደና የህዝብ ሀብት በጥቂቶች እየተቦጠቦጠ መሆኑን ያመላክተናል።

ሁለተኛውና ትኩረት የሚሻው ደግሞ በኮንስትራክሽን ጨረታ ሂደትና በግንባታ ወቅት የፕሮጀክት ተዋናዮች በሙሉ ከፍተኛ የሙያ ሥነምግባር ተላብሰው የድርሻቸውን ኀላፊነት ሊወጡ ይገባቸዋል። ከላይ በሰፈረው ነጥብ መሠረት በዘርፉ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የሙያ ሥነምግባር ችግር አለ ማለት ነው። ይኸውም የሥነምግባር ችግር በዋናነት የሚገለፀው ደግሞ የጨረታ ሂደቱ ላይ ነው። ምን ዓይነት የሥነምግባር ችግር? የሚለውን ከምንሰማውና ከምናየው አንድ ማሳያ አጃቢና ታጃቢ በመባል ይታወቃል። አንድ የግንባታ ፕሮጀክት ለጨረታ ሲቀርብ ለመወዳደር ሰነዱን የገዙት በርከት ካሉ ያንን ጨረታ ማሸነፍና ፕሮጀክቱን መሥራት የፈለገው ኮንትራክተር ከአጫራቹ በውስጥ በደረሰው መረጃ መሠረት ለጨረታው መከፈት የሚያበቁ ከ3 በላይ ተጫራቾች እርሱን ለማጀብ ሲሉ ብቻ ሰነድ እንዲገዙ ያደርግና ከውስጥ በደረሰው የፕሮጀክት ጠቅላላ ወጪ ግምት (engineering estimation) መሠረት 5 የራሱን ዋጋ አስተካክሎ በመሙላት የሌሎች ጓደኞቹን (አጃቢዎችን) ዋጋ (under) ከጠቅላላ ዋጋ በታች እና (over estimation) ከጠቅላላ ዋጋ በላይ በማድረግ ይሞላና ማህተማቸውን አድርገው እንዲያስገቡለት ያደርጋል።

ከዚህም አልፎ በውድድሩ ለመሳተፍ የተመዘገቡት የበዙና የማጀብና የመታጀብ የጥቅም ግንኙነት የሌላቸው ተጫራቾች ከሆኑ በጨረታው ዕለት የፕሮጀክቱን ጠቅላላ ዋጋ የተወሰነ ፐርሰንት በጥሬ ገንዘብ ለእነርሱ በማከፋፈል ከውድድሩ እንዲወጡ የሚያደርጉበት ግልጽ የሆነ የሥነምግባር ችግር ነው። አንዳንድ አሰሪዎች ደግሞ በተለይ እነዚህኞቹ በአብዛኛው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ናቸው። በነፃ ገበያ የኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ሆነውና ፍትሃዊ ውድድር ሊኖር ግድ በሆነበት ሀገር ውስጥ ቁጭ ብለው ሕጋዊ ለመምሰል ሲሉ ብቻ ጨረታ ቢያወጡም የጨረታው ተጋባዦች ግን በፊት እነርሱ ጋር ሠርተው የሚያውቁትና እንዲሠሩ የተፈለጉት ብቻ ናቸው። ለምሳሌ የጨረታ ሕግ ጠበቅን ለማለት ለ1 ፕሮጀክት 5 ተቋራጮችን ቢጋበዙም ይህም ሆኖ ደግሞ ሌላም አሻጥር በድርጅቱ መሐንዲስና በሥራ ተቋራጩ በኩል ይፈፀማል።

ጨረታው የሚወጣለት ፕሮጀክት ኃላፊ የሆነው መሐንዲስ ለለመደውና ከዚህ ቀደም በጥቅም ለተሳሰረው ተቋራጭ የፕሮጀክቱን ሚስጥሮችና ዋጋ አሳልፎ በይሰጠዋል ብቻ ሳያበቃ የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ወጪ (Engineering estimation) በተቋራጩ ተዘጋጅቶ ለመሐንዲሱ ይላክና የአሠሪው መሥሪያ ቤት መሐንዲስ የጨረታው አካል እንዲሆን ያደርገዋል። ከዚያም ተቋራጩ ራሱ ያዘጋጀው ዋጋ ጨረታ ሆኖ በመውጣቱ የሚወድቅበት መንገድ አይኖርም ማለት ነው። ሙስናውም እንዲህ እንዲህ እያለ ይደራል ማለት ነው። ከዚህ በላይ የሥነምግባር ችግርና የድህነት ነቀርሳነት ከወዴትስ ሊገኝ ነው ብለን ሳናበቃ ሌላም መመልከት እንችላለን።

ሌላው ከጥራት ጋር መያያዝ ያለበትና መፍትሄ ሊበጅበት የሚገባው ነጥብ ደግሞ አስገዳጅ የሆነና የኮንስትራክሽን ዘርፉን የጥራት ደረጃ እያወረደው የሚገኘው በኮንክሪት ሙሌት ጊዜ የሚከናወነው ተግባር ነው። በተለይም በቤት ልማት ፕሮጀክቶችና አነስተኛ የሕንፃ ግንባታዎች በኮንክሪት ሙሌት ፍተሻው (Test) የሚከናወነው በየደረጃው በ7 በ14 እና ከ21ኛው ቀን በኋላ መሆኑና ተቋራጩም ያን ያህል አርማታ ሲሞላ እንደማያፈርሰው ተገንዝቦ ችግር ካለ እንኳ ለተቆጣጣሪው ገንዘብ ሰጥቶ እንደሚያልፍና ተቆጣጣሪውም ቢሆን ችግር ቢኖር ያን ያህል የቆየ ኮንክሪት አፍርስ እንደማይልና የሚገባውን እንደሚቀበል አምኖ የሚተገብሩት ፀያፍ ተግባር በመሆኑ የፍተሻውና ቴስት ሥራው እንዴት ባለ አካሄድ መፈፀም እንዳለበት የኮንስትራክሽን ዘርፉ ተቋም መፍትሔ ቢያበጅለት ጥሩ ነው።

አገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ በተለይም ብዙ የሚጠበቅበት የኮንስትራክሽን ዘርፍ ለእያንዳንዷ ሀብትና ንብረት ዋጋ በመስጠት ሀገሪቱ ያላትን ውስን ጥሪት በሚፈለገው ቦታና ጊዜ በተገቢ ሁኔታ ማዋል ይጠበቅበታል። በሌሎች ዘርፎች ያለው ጅምር የሚያበረታታ ቢሆንም በተለይም በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያዎች እና ሥራ ተቋራጮች የመንግሥት ፕሮጀክቶች ወጪ ቆጣቢና ጥራት ባለው መልኩ እንዲከናወኑ ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው በመሥራት በኩል አሁንም ብዙ የሚቀራቸውና ከሙስና ጋር የተያያዙ የቤት ሥራዎች ያሉባቸው ከመሆኑ አንፃር አሁን የተጀመረውን ውይይት አጠናክሮ መቀጠልና በተመረጡ የሥጋት ቀጣና (Sensitive areas) በሆኑ የዘርፉ እንቅስቃሴዎች ላይ ስልጠና ከመስጠት ጀምሮ አስፈላጊ የሆኑ ክትትሎች በማድረግ እርምጃ የመውሰድና የማስወሰድ ጉዳይ ለነገ የሚባል መሆን የለበትም።

ሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች እንዲሁም በኮንስትራክሽን ዘርፍ በጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተሰማርተው የሚገኙ ዜጎች የፀረ-ሙስና ትግሉ አካል መሆን ያለባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በኮንስትራክሽን ዘርፍ ዓለማችን የደረሰችበትን ደረጃ የዲጂታል ግንኙነት ስርዓት መከታተልና ራሳቸውን ማብቃት እንደዚሁ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆን ከሚያስችሉ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ መሆኑን ሊረዱት ይገባል።

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር




በዚህ አምድ በዋናነት ትኩረት የሚደረገው ማንኛውም የመንግስትና የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው በማስገኘት እና በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት በማድረስ በተሰጠዉ ኃላፊነት ከሌላ ሰው ላይ ጥቅም የተቀበለ፣ የጠየቀ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም በማስገኘት የተሰጠዉን ስልጣን፣ የህዝብ አደራ ያላአግባብ የተገለገለ፤ ለሌላ ሰው ያስገኘ፣ በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ ለመንግስትና ለህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም የሰጠ፣ ያቀረበ እንደሆነ፤ በአግባቡ ለተፈጸመ የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግሰት ልማት ድርጅት እና የህዝባዊ ድርጅት ስራ የማይገባ ጥቅም ለማንኛውም ሰዉ የሰጠ፣ ከማንኛዉም የመንግስት እና ህዝባዉ ድርጅት ሰራተኛ የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ፈጻሚነት ተጠያቂ በመሆን በምርመራ የሙስና ወንጀል ፈፅመው የተገኙ አካላትን በማጠናቀር መረጃዎችን ለአንባቢያን ተደራሽ የሚደረግበት ነው።

በመሆኑም ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሁለት ደንበኞች ሒሳብ ከ5 ሚሊየን ብር በላይ ቀንሰው ለሌላ ግለሰብ በማዘዋወር ወጪ አድርገዋል የተባሉ ስምንት ግለሰቦች ላይ የሙስና ወንጀል ክስ ተመስርቷል። በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ክስ ከተመሰረተባቸው መካከል 1ኛ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የእንዶዴ ቅንጫፍ ባንክ ትሬኒ በረከት መኮንን ረዳ፣ 2ኛ በእንዶዴ ቅንጫፍ ሲኒየር ባንኪንግ አፊሰር ሁንዳአል ታደሰ ኡርጌ፣ 3ኛ በእንዶዴ ቅንጫፍ ጁኒየር አፊሰር ፋሲካ አዳሙ ለኩ፣ 4ኛ በእንዶዴ ቅንጫፍ ጁኒየር አፊሰር በቀለ ከበበ ገዳ እና በእንዶዴ ቅርንጫፍ ባንኪንግ መኮንን አሸናፊ ዘውዴ ማሞ ይገኙበታል። ቀሪዎቹ ማለትም ከ6ኛ እስከ 8ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተከሳሾች ደግሞ በግል ስራ የሚተዳደሩ ናቸው።

የፍትሕ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ በተከሳሾቹ ላይ የተሳትፎ ደረጃ ጠቅሶ የሙስና ወንጀል ክስ አቅርቧል። ከ1ኛ እስከ 4ኛ ተራ ቁጥር በተጠቀሱ ተከሳሾች ላይ ብቻ በቀረበው ክስ ተከሳሾቹ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 9/1/ሀ/ እና /2/ ስር የተመለከተውን ተላልፈዋል የሚል ነው። በዚህም ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተከሳሾች ግብይት ያለአግባብ በማጽደቅ፣ በቀረበ ሀሰተኛ የነዋሪነት መታወቂያ ሒሳብ መክፈትና ቅድመ ኦዲት ያለአግባብ ማድረግ የሚል የተሳትፎ ደረጃ የተጠቀሰባቸው ሲሆን፥ አንደኛ ተከሳሽን በሚመለከት ግን ከባንኩ መመሪያና አሰራር ውጪ ከሁለት ደንበኞች ሒሳብ ተቀናሽ በማድረግ በ6ኛ እና በ7ኛ ተከሳሾች ሒሳብ የደንበኞችን ገንዘብ ያለአግባብ ማዘዋወር የሚል ክስ ቀርቧል።

በአጠቃላይ የባንኩን መመርያና አሰራር በመጣስ የተሰጣቸውን ሥልጣን ወይም ኃላፊነት በግልጽ ተግባር ያለአግባብ በመገልገል ከሌሎች ካልተያዙ ግለሰቦች ጋር በመመሳጠር የባንኩ ደንበኞች ከሆኑት 1ኛ አቶ አብርሃ ገብሬ ከተባሉ ግለሰብ ሒሳብ ላይ በተለያዩ ቀናት 3 ሚሊየን 41 ሺህ 165 ብር እንዲሁም ከሁመራ ከተማ ስፖርት ምክር ቤት ሒሳብ ደግሞ 2 ሚሊየን 576 ሺህ ብር በመቀነስ በድምሩ 5 ሚሊየን 817 ሺህ 180 ብር ወደ 6ኛ እና 7ኛ ተከሳሾች ያለአግባብ ገቢ በማድረግ በደንበኞቹ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሱ መሆኑ ተጠቅሶ፥ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በሥልጣን አላግባብ መገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል ተከስሰዋል።

5ኛ ተከሳሽን በሚመለከት ደግሞ ተከሳሹ በባንኩ እንዶዴ ቅርጫፍ ሲሰራ ገንዘቡ የወንጀል ፍሬ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው በ1ኛ ተከሳሽ አማካኝነት ለ7ኛ ተከሳሽ ከተዘዋወረ ገንዘብ ውስጥ ለ4 ግለሰቦች እና በአንድ የግል ድርጅት ስም ወደ ተከፈተ ሒሳብ በተለያየ የገንዘብ መጠን ያዘዋወረና 50 ሺህ ብር በጥሬ ያወጣ መሆኑ ተጠቅሶ፥ የንብረቱን ህገ-ወጥ ምንጭ ለመደበቅ ወይም ለመሸፈን በማሰብ ገንዘቡን በይዞታው ያደረገ፤ የተጠቀመ እና ያስተላለፈ በመሆኑ በወንጀል የተገኘን ገንዘብን ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀል ተከስሷል።

6ኛ ተከሳሽ ደግሞ ከቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 11 የተሰጠ የሚል ሀሰተኛ የነዋሪነት መታወቂያ በመገልገል መስፍን ተፈራ በሚል ስም የባንክ ሒሳብ የከፈተና መንግስታዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፤ ወደ ሀሰት መለወጥ ወይም በሀሰት በመገልገል ከግል ተበዳይ በአቶ አብርሃ ገብሬ እና ከሁመራ ከተማ ስፖርት ምክር ቤት ሒሳቦች ተቀንሶ በ1ኛ ተከሳሽ አማካኝነት ወደ ሒሳቡ የተዘዋወረለትን ገንዘብ በተለያዩ ቀናቶች ወጪ በማድረግ 190 ሺህ 15 ብር ወደ አቶ ጌትነት ውቤ አደራ ወደተባለ ግለሰብ ሒሳብ ያዘዋወረ በመሆኑ ገንዘቡን በይዞታው ያደረገ፤ የተጠቀመ እና ያስተላለፈ በመሆኑ በፈፀመው በወንጀል የተገኘን ገንዘብን ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀል ተከስሷል። 7ኛ ተከሳሽ በሚመለከት ደግሞ ወደ ሒሳቡ በ1ኛ ተከሳሽ አማካኝነት የተዘዋወረለትን ገንዘብ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብን ወይም የንብረቱን ህገ-ወጥ ምንጭ ለመደበቅ ወይም ለመሸፈን በማሰብ 2 ሚሊየን 300 ሺህ 120 ብር ያለአግባብ ገቢ የተደረገለትን ገንዘብ በሙሉ ለ5ኛ ተከሳሽ ሒሳብ በቁጥር ያዘዋወረ በመሆኑ በፈፀመው በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ሕጋዊ አድርጎ ማቅረብ ወንጀል ተከስሷል።

8ኛ ተከሳሽ ላይ በተመሳሳይ የሙስና አዋጁ በአንቀጽ 23/ ንዑስ ቁጥር 3 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የባንኩ ደንበኛ የሆኑት አቶ አብርሃ ገብሩ የተባሉ ግለሰብ ሒሳብ ቁጥር ውስጥ ብር 3 ሚሊየን 241 ሺህ 180 ብር መኖሩን እና ሒሳቡ የማይንቀሳቀስ መሆኑን በማጥናት አቶ አብርሃ ገብሬ የተባሉ ደንበኛን ስም በመጠቀም ወካይ ሆኖ በመቅረብ እራሱ ተወካይ ሆኖ የራሱን ፎቶግራፍ በመጠቀም በደንበኛው ውክልና ሳይሰጥ ውክልናው በደንበኛው የተሰጠ መሆኑን የሚገልጽ ሀሰተኛ ውክልና ማቅረቡ በክሱ ተመላክቷል። ከ1ኛ እስከ 5ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተከሳሾች ችሎት ቀርበው በዚህ መልኩ የቀረበባቸው ክስ በችሎት ከደረሳቸው በኋላ የዋስትና መብታቸውን እንዲከበር ጠይቀዋል። ፍርድ ቤቱም ከ1ኛ እስከ 4ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተከሳሾች የቀረበባቸው የክስ ድንጋጌ ዋስትና እንደማያስፈቅድ ገልጾ ጥያቄያቸውን

ከገፅ 17 የዞረ



# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

ውድቅ አድርጎል። 5ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበው ድንጋጌ ዋስትና የማያስከለክል ባለመሆኑ የዋስ መብቱ ተጠብቋል። ፍርድ ቤቱ በችሎቱ የቀረቡ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት የክስ መቃወሚያ እና ያልቀረቡ ቀሪ ተከሳሾችን ለመጠባበቅ ለጥር 8 ቀን 2016ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቷል።

በሌላ መረጃ 1 ሚሊየን ብር ጉቦ ሲቀበል እጅ ከፍንጅ ተይዟል በተባለው የጉምሩክ ትራንዚስተር (አስተላላፊ) ላይ የሙስና ወንጀል ክሥ ተመሰረተ። ክሱ የተመሰረተው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ሲሆን፥ ተከሳሹ የጉምሩክ ትራንዚስተር (አስተላላፊ) ግዑሽ አዳነ አበራ እንደሚባልም ተመላክቷል። የፍትኅ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬቶሬት ዐቃቢ-ሕግ ተከሳሹን የሙስና ወንጀል አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 27 ሥር የተደነገገውን ድንጋጌ ተላልፏል በማለት በተከሳሹ ላይ የሙስና ወንጀል ክስ አቅርቦበታል። በዚህም ባቀረበበት የሙስና ወንጀል ክስ ዝርዝር ላይ እንደተመላከተው ተከሳሹ በሚሰራው የጉምሩክ አስተላላፊነት ስራ መሰረት ከቀረጥ ነጻ ለኢንቨስትመንት የገባን "ቶዮታ ሀይሉክስ" ተሽከርካሪ÷ ነብዩ ቡሽራ ጅማ ከተባለ የግል



ተበዳይና 1ኛ የዓቃቢ ሕግ ምስክር ከሆነው ግለሰብ ጋር በመሆን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለመፈፀም በመስማማት የግል ተበዳይን የሰባት ዓመት የመኪናውን ቀረጥ እና ታክስ 1ሚሊየን 511 ሺህ 356 ከ66 ሣንቲም እንዲከፍሉና ተሽከርካሪውን በአካል እንዲያቀርቡ መናገሩን ዐቃቤ ሕግ በክሱ ዝርዝር ላይ አስፍሯል።

ከዚህም በኃላ የግል ተበዳይ በኅዳር 24 ቀን 2016 ዓ/ም ልዩ ቦታው ሳሪስ አቦ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ከሚገኘው የጉምሩክ ኮሚሽን መሥሪያ ቤት ሲቀርቡ ተከሳሹ ተሽከርካሪው ለጥያቄ እንደሚፈለግ እና መሿለኪያ ኃይሌ ይርጋ ሕንጻ ላይ በሚገኘው የጉምሩክ ዋና መሥሪያ ቤት መጠየቅ እንዳለባቸው መግለጹም ተጠቅሶ በክሱ ዝርዝር ተካቷል። በዚህ መልኩ ተሽከርካሪው እንዲለቀቅ ከጉምሩክ ኮሚሽን ኃላፊዎች ጋር እንደሚያደራድራቸው ለግል ተበዳይ በመንገር እና መኪናውን ለመልቀቅ የግል ተበዳይ 1 ሚሊየን ብር እንዲከፍሉ ኃላፊዎች መግለፃቸውን በማሳወቅ በኅዳር 30 ቀን 2016 ዓ/ም በግምት ከቀኑ 7 ሠዓት ከ30 አካባቢ ቦሌ መድሃኒያለም አከባቢ ልዩ ቦታው አኬኸ‍ዥን ካፌ ውስጥ ከግል ተበዳይ ጋር በመገናኘት 1 ሚሊየን ብር በአቢሲኒያ ባንክ የተጻፈ ቼክ ሲቀበል እጅ ከፍንጅ የተያዘ በመሆኑ በክሱ ተጠቅሶ ዐቃቢህግ የማቀባበል የሙስና ወንጀልክስ አቅርቦበታል። ዐቃቤ ሕግ ከክስ ዝርዝሩ ጋር የሰውና የሠነድ ማስረጃ አያይዞ አቅርቧል። ተከሳሹ ችሎት ቀርቦ ክሱ እንዲደርሰው ከተደረገ በኋላ የክስ ዝርዝሩ በችሎት በንባብ ተሰምቷል።

በሌላ የሙስና እና ብልሹ አሰራር መረጃ የኦሮሚያ ክልል ከፍተኛ ባለስልጣን ዘመድ እንደሆኑ በማስመሰልና ሲሚንቶ አስመጪ ነን በሚል በማታለል ገንዘብ ተቀብለዋል የተባሉ ተከሳሾች በጽኑ እስራትና በገንዘብ ተቀጠዋል። የቅጣት ውሳኔውን የወሰነው የኦሮሚያ ክልል የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው። ተከሳሾቹ የስንቄ ባንክ ፍቼ ቅርጫፍ የደንበኞች አገልግሎት ኃላፊ እንዳለ ዋቅቶላ እና የትዳር አጋሩ ወ/ሮ ሀዊ ፋጂ ናቸው። የክልሉ የሰሜን ሸዋ ዞን ዐቃቤ ሕግ ክስ እንደሚያስረዳው 1ኛ ተከሳሽ የትዳር አጋሩ የሆነችው 2ኛ ተከሳሽ አንድ የኦሮሚያ ክልል ከፍተኛ ባለስልጣን እህት እንዲሁም ሌላ ባለስልጣን ደግሞ አጎቷ እንደሆነ ለተለያዩ ግለሰቦች በመንገርና በሀሰት እምነት እንዲጥሉባት አድርጓል በማለት ዐቃቤ ሕግ በክሱ አስፍሯል። 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ ከዳንጎቴ ሲሚንቶ ፋብሪካ ሲሚንቶ አስመጣለሁ በማለት በተለያዩ ጊዜያት ግለሰቦችን በማታለል በ2015 ዓ.ም ከአንድ የግል ተበዳይ 960 ሺህ ብር ከሌላኛው የግል ተበዳይ ደግሞ 600 ሺህ ብር በባንክ ሂሳቧ ገቢ እንዲደረግላት ማድረጓ ዐቃቤ ሕግ በክስ ዝርዝሩ ገልጿል። ሁለቱም ተከሳሾች የሙስና አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32 ንዑስ ቁጥር 2 ስር የተደነገገውን ድንጋጌ በመተላለፍ በአታላይነት ወንጀል ተከሰዋል። ተከሳሾቹ ክሱ ከደረሳቸው በኋላ ወንጀሉን አለመፈጸማቸውን ጠቅሰው የሰጡትን የዕምነት ክህደት ቃል ተከትሎ ዐቃቤ ሕግ የሰውና የሰነድ ማስረጃ አቅርቦባቸዋል። ፍርድ ቤቱም የዐቃቤ ሕግን መከራከሪያ ማስረጃን መርምሮ ተከሳሾቹ በተከሰሱበት ድንጋጌ እንዲከላከሉ ብይን የሰጠ ቢሆንም ተከሳሾቹ የመከላከያ ማስረጃ እንደሌላቸው ገልፀዋል። ፍርድ ቤቱም የጥፋተኝነት ፍርድ በመስጠት የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት መርምሮ ተከሳሾቹን በ7 አመት ከ8 ወራት ጽኑ እስራትና በ20 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል።

በሌላ የሙስና ወንጀል መረጃ ሀሰተኛ የሆነ የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ማስረጃ በመጠቀም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አምቦ ዲስትሪክት የስራ ቅጥር ፈጽመዋል የተባሉ ግለሰቦች በእስራት እንዲቀጡ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት ወሰነ። ተከሳሾቹ ወንጀሉን መፈጸማቸውን አምነው ለችሎቱ ቃላቸውን መስጠታቸውን ተከትሎ ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ማስረጃ መስማት ሳያስፈልገው በተከሳሾቹ ላይ የጥፋተኝነት ፍርድ አስተላልፏል። የኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ የሙስና አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23 ስር የተመላከተውን ድንጋጌን ተከሳሾቹ ተላልፈዋል በማለት ሀሰተኛ መንግስታዊ ወይም ህዝባዊ ሰነዶችን አዘጋጅቶ መጠቀም የሙስና ወንጀል ክስ አቅርቦባቸው ነበር።

ክሱ የቀረበባቸው ተከሳሾች በአጠቃላይ 12 ሲሆኑ፤ ከነዚህ መካከል ባጂጌ ከበደ፣ ግርማዬ ደገፉና በሬዳ ነበራ ይገኙበታል። የቀረበው ክስ ላይ እንደሚያመላክተው ተከሳሾቹ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አምቦ ዲስትሪክት በወጣ የስራ ማስታወቂያ የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ማስረጃ በማቅረብ የስራ ቅጥር ውል ስምምነት መፈጸማቸው በክሱ ተጠቅሷል። ከተከሳሾቹ መካከል 10ሩ የቅጥር ውል ከፈጸሙ በኋላ ለ10 ወራት በየደረጃው በተለያዩ መጠን ወርኃዊ ደመወዝ መውሰዳቸውን ዐቃቤ ሕግ በክሱ አመላክቷል። ቀሪዎቹ ማለትም ሁለት ተከሳሾች ደግሞ የስራ ቅጥር ውል ስምምነት ከፈጸሙ በኋላ የማስረጃ ማጣራት ስራ ሲጀመር መሰወራቸው ዐቃቤ ሕግ በክሱ አመልክቷል። በዚህም መልኩ ዐቃቤ ሕግ ሀሰተኛ መንግስታዊ ወይም ህዝባዊ ሰነዶችን አዘጋጅቶ መጠቀም የሙስና ወንጀል ክስ አቅርቦባቸዋል።

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት በተከሳሾቹ ላይ የቀረበው ክስ ዝርዝር ለተከሳሾቹ እንዲደርስ በማድረግ የክስ ዝርዝሩ በችሎት በንባብ አሰምቶ ነበር። ዐቃቤ ሕግ ከክሱ ጋር ለወንጀሉ መፈጸም ያስረዱልኛል ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አያይዞ አቅርቧል። የዋስትና መብታቸው ታግዶ ማረሚያ ቤት እንዲወርዱ ብይን የተሰጠባቸው ተከሳሾቹ በማረሚያ ቤት ሆነው ጉዳያቸውን ተከታትለዋል። በዐቃቤ ሕግ የቀረበባቸው የክስ ዝርዝር እንዲሻሻልላቸው ተከሳሾች የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ ቢያቀርቡም፤ ዐቃቤ ሕግ ክሱ ግልጽ መሆኑን ጠቅሶ ሊሻሻል አይገባም የሚል መልስ በጽሁፍ አቅርቧል።

ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን መርምሮ የክስ መቃወሚያ ጥያቄው ክሱ እንዲሻሻል የሚያስችል የህግ መሰረት የለውም በማለት ውድቅ አድርጓታል። ከዚህም በኋላ ተከሳሾቹን የዕምነት ክህደት ቃላቸውን እንዲሰጡ ተደርጎ ተከሳሾቹ የወንጀል ተግባሩን መፈጸማቸውን አምነው ለችሎቱ ቃላቸውን ሰጥተዋል። በዚህም ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ምስክር መስማት ሳያስፈልገው በተከሳሾቹ ላይ በተከሰሱበት ድንጋጌ የጥፋተኝነት ፍርድ አስተላልፏል። ተከሳሾቹ በክሱ ላይ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት በማመናቸው፣ የቀደመ የወንጀል ሪከርድ አለመኖሩንና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን በቅጣት ማቅለያ ታሳቢ በማድረግ ፍርድ ቤቱ እያንዳንዳቸውን በ1 አመት ከ 8 ወራት እስራት እንዲቀጡ ወስኗል።

# ኪነ-ጥበብ

# ልጓም ነው!




ግራና ቀኝ ወጥሮ ተብትቦ አጥብቆ አሳሪ፣
ወደኋላ ጎትቶ ከፊት መንገድ አስቀሪ፣
ሰላምና ተስፋን ፍቅርን በእሾህ አጣሪ፣
ጦርነትና ሽብርን ሌብነትን ቆፋሪ፣
ግብረ-ግብና ትህትናን መልካም ምግባርን ቀባሪ፣
ልጓም ነው እርሱ ሙስና ድምጽ አልባ አሸባሪ።

ሀገርን እንዳትበለጽግ መረብ ወጥሮ የያዘ፣
ሰላምን ጨፍልቆ በሌብነት የደለዘለ፣
በውስብስብ ድርጊቱ ጥሩ ሥራን ያፈዘዘ፣
የሀገርን ኢኮኖሚ ላይራመድ የገነዘ፣
ልጓም ነው እርሱ ሙስና

በጨለማ በስውር ሀገርን የገዘገዘ።
ሙስና ልጓም ነው እድገት የሚገታ፣
በድበቅ የሚገል የካንሰር በሽታ፣
አንጋዶ የሚጥል የምግብን ገበታ፣
እዚህ የለም ሲሉት ያለ ሁሉ ቦታ፣
ሙስና ገዳይ ነው

በሰፊ መዳፉ ሀገር የሚመታ።
ሙስና ጥልቅ ነው ረጅም ነው ስሩ፣
ድርጊቱ ረቂቅ ድብቅ ነው ሚስጢሩ፣
ቶሎ የሚሰፋ ጥልፍልፍ ነው ድሩ፣
ውድቀት የሚያመጣ መጨረሻ ግብሩ፣


ልጓም ነው ሙስና ይህ ነው ተግባሩ፣
ሙስና ማነቆ ሙሰና ልጓም ነው፣
የእድገት ጉዳና የእሾህ አጥር ነው፣
እባካችሁ ሰዎች ሙስና ልጓም ነው፣
ብዙ ነው ዝርዝሩ አያልቅም
ብንገልጸው፣

ይልቁንም ደግሞ መፍትሄ የሚሆነው፣
ትልቅ ትንሽ ሳንል ሥራችን አረገነው፣
ችግሩን ተረድተን መንሰኤውን አውቀነው፣
ተባብረን በጋራ በአንድ እንታገለው።

ከያብባል አዲስ

# መልካም ዜጋ

## በመልካም ሥነምግባር የታነፀ ትውልድ ማፍራት ለሀገር እድገት አስተዋፅኦው የጎላ ነው !



በስህተት ወደ ባንክ አካዉንቱ የገባዉን 1.1 ሚሊዮን ብር የመለሰዉ ወጣት ተማሪ አዲስ አለም ኤርሚያስ ቤተሰቦቼ፣ ሐይማኖቴ፣ ትምህር ቤቴ እና ያደኩበት ማህበረሰብ ያስተማረኝ ይህንን ነው። ወጣት አዲስአለም ኤርምያስ የጎጎታ ኬር ሂጋ ሞዴል አዳሪ ትምህርት ቤት ተማሪ ሲሆን በስም መመሳሰል ወደ አካወንቱ የገባውን 1.1 ሚሊየን ብር በታመኝነት መመለሱ ታውቋል። በታህሳስ 11/2016 ዓ.ም ከጓደኞቹ ጋር በነበረበት ከረፋዱ 5 ሰዓት 1.1 ሚሊየን ብር ከኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ (CBO) ወደ አካውንቱ መግባቱን የሚያሳይ መልዕክት ይደርሰዋል።

በሰዓቱ የመደናገጥ ስሜት ቢፈጥርብኝም እራሴን አረጋግቼ ከጓደኞቼ ጋር በጋራ መክሬ ብሩ በአስቸኳይ ወደ ባንኩ መመለስ እንዳለበት ተማምነን ወደ ኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ ( ዱራሜ ቅርንጫፍ) ሪፖርት ለማድረግ ሄድን ያለው ገንዘቡን መልሻለው የሚለው ተማሪ ኤርሚያስ በኔ መዘናጋትና ቸልተኝነት ምክኒያት ምናልባትም ለህክምና የተፈለገ ብር ሆኖ ሕይወት እንዳይጠፋ ጭምር በማሰብ እና እራሱን በእሱ/በእሷ ቦታ አድርጎ በማሰብ ለባለቤቱ እንዲመለስ ማድረጉን ተናግሯል። አዲስአለም አያይዞም ቤተሰቦቼ፣ ሐይማኖቴ ትምህር ቤቴ እና ያደኩበት ማህበረሰብ ያስተማረኝ ይህ ነው ይላል። የሰው ሀቅ መውሰድ ከጥቅሙ ጉዳቱ የሚያመዝን መሆኑን በመረዳት በስም መመሳሰል የገበውን ብር ለባለቤቱ እንዲመለስ ማድረጉን ጨምሮ ገልጿል።

ከዚህ ወጣት የምንማረው በመልካም ሥነምግባር ተኮትኩቶ ያደገና ግበረ-ገብን የተላበሰ መሆኑን ነው። ለዚህ መነሻ የሆነው ደግሞ እርሱም እንደገለፀው ያሳደገው ቤተሰብና ማህበረሰብ፣ ያስተማረው ት/ቤት እና ቤተ እምነት በመልካም ምግባር ስለሆነ ነው። ለልጆች የመልካም ስብዕና ባለቤት መሆን ከቤተሰብ በእጅጉ የሚጠበቅ ጉዳይ ነው። ሥነምግባርን ተላብሶ ያደገ ልጅ መልካም አስተሳሰብ ያለውና መልካም የሚባልን ነገር የሚያደርግ ነው። ቤተሰብ የአንድን ማኅብረሰብ እጣ ፈንታ ለመወሰን የሚችል የሚታይና የሚዳሰስ ተቋም ነው። ጥሩ ቤተሰብ የጥሩ ማኅበረሰብ መሠረት ነው። ጥሩ ማኅበረሰብ የጥሩ  ሀገር መሠረት ነው። ስለዚህ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የሚኖር ግብረገባዊ መስተጋብር እናት ወይም አባት (የቤተሰብ ኃላፊዎች) ልጆቻቸውን በሥነምግባር ለመቅረጽ የሚኖራቸው ኃላፊነት እና አደራ እጅግ ከባድ ነው። በማኅበረሰቡ ውስጥ በረዥም የጊዜ ሂደት የሚፈጠሩ የጋራ እሴቶች፣ ባህሎች እና ማንነቶች ትውልድን ለማነጽ እጅግ ወሳኝ ናቸው።  ጥሩ ሥነምግባር ባለው ማህበረሰብ ውስጥ ያደገ ሰው ጥሩውን ሥነምግባር ይዞ ይጓዛል።

በሌላ መልኩ ትምህርት ቤት አንድን በመልካም ሥነምግባር  የታነፀ ዜጋ ለመፍጠር የሚያስችል ተቋም ነው። ሥነምግባርን በጥሩ ሁኔታ ለመገንባት በትምህርት ቤት ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ ተጠናክሮ መሰጠት ይኖርበታል። በዚህ ረገድ ሌላው የሚጠቀሰው የኃይማኖት ተቋም ነው። ሁሉም ሃይማኖቶች መልካምና በመንፈስ የበለፀገ ትውልድን ለማፍራት የሚያስችል አስተምሮት አላቸው። ምክንያቱን ሁሉም ሃይማኖቶች ልዕለ ኃያል የሆነ ተፈጥሮ ያላቸው ቸር፣ ሩህሩህ፣ አዛኝ፣ ቀና፣ ሁሉንም እኩል የሚያይ፣ ተንኮልንና ክፋትን የሚጠላ፣ ጠጭነትን፣ ሴሰኝነትን፣ ቦዘኔነትን የማይወድ ወዘተ ፈጣሪ ወይም አምላክ  አላቸውና። አስተምሮታቸውም በእነዚህ የመንፈስ ማጽጃ ጉዳዮችና ሌሎች ቀኖናዎች ላይ የተመሠረቱ ናቸው። በየትኛውም የሃይማኖት ተቋማት የሚሰጡ መንፈሳዊ አስተምሮዎች መልካም ሥነምግባርን በተለይም ግብረ-ገብን የሚሰብኩ ናቸው። ስለሆነም ማንኛውም የሀይማኖት ተቋም በምዕመናቸው (ተከታዮቻቸው) ላይ መልካም የሆነ ሥነምግባርን መትከል የሚችሉ ናቸው። በመሆኑም የአንድ ትውልድ ሥነምግባር በቅጡ ይታነጽ ዘንድ እኒህ ተቋማት መሰረት ናቸው።

